‹‹ነፍሴ እግዚአብሔርን ታከብረዋለች፤ መንፈሴም በአምላኬ፣ በመድኃኒቴ ሐሤትን ታደርጋለች››

(ሉቃ.፩፥፵፯)

# ስምዐ ጽድቅ

## ማውጫ


፪ አጫጭር ዜናዎች

፬ መልእክት

፮ ሪፖርታዥ

፰ ቤተ አብርሃም

፲፪ ቃለ መጠይቅ

፲፭ የሕፃናት ዓምድ

፲፯ ትዝብት

፲፱ ምሥጢሬን ላካፍላችሁ




## ስምዐ ጽድቅ


የቤተ ክርስቲያኒቱን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓትና ትውፊት ጠብቆ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ማኅበረ ቅዱሳን በኅትመት ሚዲያ መምሪያ እየተዘጋጀ በወር ሁለት ጊዜ የሚወጣ መንፈሳዊ ጋዜጣ

ጳጉሜን ፫ ቀን ፲፱፻፹፫ ዓ.ም. ተጀመረ



☎ 011-1553555/ 011-1553442

✉ 80078

አዲስ አበባ

ምክትል ዋና አዘጋጅ

ወርቅነሽ ቱፋ

ከፍተኛ ሪፖርተር

ካሣሁን ለምለሙ

የገጽ መልክ (Layout) ዲዛይነርና ጸሐፊ

ገነት ታደሰ

የዝግጅት ክፍሉ ኢሜይል

newspaper@eotcmk.org



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ

# በነጻነትና በእኩልነት ለመኖር ሰላም ከፍተኛ ዋጋ ሊሰጠው እንደሚገባ ተገለጠ

ካሳሁን ለምለሙ

በሀገራችን ኢትዮጵያ በፍቅር፣በአንድነት፣በነጻነትና በእኩልነት ለመኖር ሰላም ከፍተኛ ዋጋ ሊሰጠው እንደሚገባ ቀዳማዊ ፓትርያርክ ርእሰ ለቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለሃይማኖት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ገለጡ፡፡

ቅዱስነታቸው ይህንን የገለጡት የ፳፻፲፬ ዓ.ም የፍልሰታ ጾም መግባቱን አስመልክቶ በአሜሪካ ዋሽንግተን ዲሲ ሆነው በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ ነው፡፡

ቅዱስነታቸው በመግለጫቸው "በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ ሕዝብ ፍላጎት ፍጹም ሰላም ያላት ሀገር እንድትኖረው ነው" ካሉ በኋላ "ይሁንና ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ ሰላም ስለማይመጣ ሁሉም ሰው በያለበት በትጋት ሊጸልይ ይገባል" ሲሉ እንዲጸልይ አሳስበዋል፡፡

ቅዱስነታቸው አያይዘውም "በሀገራችን ፍጹም የሆነ ሰላም ሰፍኖ ሕዝባችን እግዚአብሔር በሰጠው ምድር በፍቅር፣ በአንድነት፣ በነጻነትና በእኩልነት እንዲኖር ኦርቶዶክሳውያን ምእመናን የቅድስት ድንግል ማርያምን ጸሎት፣ ስእለት፣ ተማኅፅኖና አስተበቍዖት አጋዥ አድርገው በልዩ ሱባዔ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ፣ ንስሓ መግባት፣ ጾም ጸሎት ማድረግ ነዳያንን መርዳትና ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን መቀበል አለባቸው" ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ቅዱስነታቸው አክለውም በሀገራችን እየተከሠቱ ያሉ ያላስፈላጊ የእርስ በርስ ግጭቶችን ሰላማዊ በሆነ መንገድ ለመፍታት እየተደረገ ያለው የሰላም ውይይት ተስፋ ሰጪ መሆኑን ተናግረው "የሰላም ውይይቱ ሥር የሰደደ፣ በተግባር የተተረጎመና በብዙ መልኩ ለተጎዳው የኢትዮጵያ ሕዝብ መጠገኛ ሊሆን ይገባል" ብለዋል፡፡

ምእመናን በዚህ የሱባኤ ወቅት ወደ እግዚአብሔር አቤት በማለት፣ ለሰላም ዘብ በመቆምና በሰላም ሂደቱ ላይ የበኩላቸውን ጥረት እንዲያደርጉ ያሳሰቡት ቅዱስነታቸው መንግሥትም ሆነ የዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ የሰላም ሂደቱን በመደገፍ ሀገርንና ሕዝብን ከጥፋት እንዲታደጉ አባታዊ መልእክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡



የግቢ ጉባኤያት ተተኪ አመራር ሥልጠና ተሳታፊዎች በከፊል

# ማኅበረ ቅዱሳን የግቢ ጉባኤያት ተተኪ አመራር ሥልጠና መስጠቱን አስታወቀ

*ካሳሁን ለምለሙ*

ማኅበረ ቅዱሳን በማህል ማእከላት ማስተባበርያ አስተባባሪነት የግቢ ጉባኤያት ተተኪ አመራሮች ሥልጠና ከነሐሴ ፩ ቀን ፳፻፲፩ ዓ.ም ጀምሮ ሲሰጥ መቆየቱን አስታወቀ፡፡

የአምስት ማእከላት ግቢ ጉባኤያት ተተኪ አመራሮችን ያካተተው ይህ ሥልጠና ተከታታይ ስድስት ቀናት ሲሰጥ መቆየቱ ተገልጿል፡፡

የሥልጠናው ዋና ዋና ይዘቶች ነገረ ቤተ ክርስቲያን፣ተግባቦት፣ወቅታዊ የቤተ ክርስትያን ጉዳዮች፣ የተማሪዎች አስተዋጽኦ እንዲሁም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስትያን በዘመናት የነበራት የመሪነት ሚና የሚሉ እንደነበሩ በአዲስ አበባ ማእከል የግቢ ጉባኤያት አገልግሎት ዋና ክፍል አስተባባሪ የሆኑት አቶ ጌትነት ገድፍ ተናግረዋል፡፡

አቶ ጌትነት አያይዘውም የግቢ ጉባኤ ተማሪዎች የክረምት የዕረፍት ጊዜያቸውን ታሳቢ በማድረግ በየዓመቱ የክረምት ወራት እንደገባ በማህል ማእከላት አስተባባሪነት የተተኪ አመራሮች ሥልጠና እንደሚሰጥ ገልጠው የዘንድሮው የግቢ ጉባኤያ ተተኪ አመራሮች ሥልጠና ግን ከዚህ ቀደም ከነበረው የሥልጠና ጊዜ ዘግይቶ በነሐሴ ወር መጀመሩን ተናግረዋል፡፡

አቶ ጌትነት አክለውም የግቢ ጉባኤያት ተተኪ አመራሮች ከሥልጠናው ዘርፈ ብዙ የመሪነት ክህሎት ግንዛቤዎችን እያገኙበት መሆኑን ተናግረው "ባገኙት የመሪነት ክህሎት ግንዛቤ ለቤተ ክርስቲያን የሚጠቅም ነገር ይሠራሉ ተብሎ ይጠበቃል" ብለዋል፡፡

የሥልጠናውን አስፈላጊነት አስመልክቶም "ዘመኑን ተከትለው በቤተ ክርስቲያን ላይ እየመጡ ያሉ ተግዳሮቶችን ተቋቁሞ ለማለፍ ብቁ የሆኑ አመራሮች የሚያስፈልጉበት ጊዜ አሁን ነው" ስትል የገለፀችው ደግሞ ሠልጣኝ ተማሪ ቤተልሔም ዘር አብዛ ናት፡፡

ሌላው ሠልጣኝ ተማሪ ዲያቆን አብዲሳ ዘመቻ በበኩሉ "የግቢ ጉባኤያት የተተኪ አመራሮች ሥልጠናን መውሰዳችን በአገልግሎት ሒደት ውስጥ የሚፈጠሩ ተግዳሮቶችን አስቀደመን እንድንረዳ ያግዘናል" ሲል ተናግሯል፡፡

# ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማቲያስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለሃይማኖት ጾመ ፍልሰታን አስመልክቶ ያስተላለፉት መልእክት

## በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን!

በሀገር ውስጥም ሆነ በመላው ዓለም ዙሪያ ለምትገኙ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምእመናንና በሙሉ እንኳን ለጾመ ፍልሰታ ለማርያም በሰላም አደረሰን አደረሳችሁ፡፡ “ወተዘከረ ሣህሎ ዘይቤሎሙ ለአበዊነ ለአብርሃም ወለዘርዑ እስከ ለዓለም፤ ለአባቶቻችን ለአብርሃምና ለዘሩ የነገራቸውን ይቅርታውን ለዘላለሙ አሰበ” (ሉቃ.፩፥፶፭ )

ማኅደረ መለኮት፣ ማኅደረ መንፈስ ቅዱስ የሆነች እናታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በመንፈስ ቅዱስ ተሞልታ እግዚአብሔርን ባመሰገነችበት ምስጋናዋ ከላይ የተጠቀሰውን ይሄንን አረፍተ ነገር መናገሯ በቅዱስ ወንጌል ተጽፎልናል፡፡ ቅድስት ድንግል ማርያም በዚህ ምስጋናዋ የገለጸችው ዐቢይ መልእክት የክብር አምላክ እግዚአብሔር የተናገረውን የማያስቀር አምላክ መሆኑን ነው፡፡ ኤልሻዳይ እግዚአብሔር የተስፋ አምላክ ነውና በየጊዜው ለፍጡራኑ የተስፋ ቃል ይሰጣል፡፡ ቃልኪዳንም ይገባል፡፡

እግዚአብሔር በክዋኔው ዘለዓለማዊ እንደሆነ ሁሉ ቃልኪዳኑም ዘለዓለማዊ እንደሆነ ‹‹ወተዘከረ ኪዳኖ ዘለዓለም፣ ማለትም ዘላለማዊ ቃል ኪዳኑን አሰበ›› በማለት ቅዱስ መጽሐፍ ያስተምረናል፡፡ እግዚአብሔር መፍቅሬ ሰብእ ከሆነ አምላካዊ ባሕርዩ በመነጨ ፍቅሩ ከመጀመሪያው ሰው ከአዳም ጀምሮ ለአበው ቃልኪዳን እንደገባላቸው ተጽፎልናል፡፡ ይልቁንም ለአብርሃም “በዘርዕከ ይትባረኩ ኵሎሙ አሕዛበ ምድር ማለትም የምድር አሕዛብ ሁላቸው በዘርህ ይባረካሉ” ብሎ ለዓለም ሁሉ የሚሆን በረከትና ድኅነት ከእርሱ እንደሚገኝ ቃል ኪዳን ገብቶለታል፡፡ ቅድስት ድንግል ማርያም ‹‹ለአብርሃምና ለዘሩ የተናገረውን ቃል አሰበ›› ብላ የገለጸችውም ይህንን ቃልኪዳን ነው፡፡ ምክንያቱም የምድር አሕዛብ ሁሉ የሚባረኩበት ዘር ኢየሱስ ክርስቶስ በወቅቱ በማሕጸኗ እንዳለ ታውቃለችና፡፡

የተወደዳችሁ የመንፈስ ቅዱስ ልጆቻችን ምእመናንና ከቅድስት ድንግል ማርያም ምስጋና የምንማረው ዐቢይ ትምህርት ሁልጊዜ የእግዚአብሔርን ድንቅ ነገር በማስተዋል በመናገርና በመመስከር ማመስገን፣ ማስብና ማስታወስ እንደሚገባን ነው፡፡ እግዚአብሔርም ይህንን እንደሚወድ ‹‹ወተዘከሩ መንክሮ ዘገብረ፤ ያደረገውን ድንቅ ሥራ ሁሉ አስቡ›› ብሎ ነግሮናል፡፡ እግዚአብሔር የተናገረውን የማያስቀር ታማኝ አምላክ ነውና ለአብርሃምና ለዘሩ የገባውን ቃልኪዳን እነሆ ከዛሬ ሁለት ሺህ ዐሥራ አምስት ዓመታት በፊት ቃልኪዳኑን እንደተስፋ ቃሉ በተግባር ፈጽሟል፡፡ የምድር አሕዛብ ሁሉ የሚባረኩበት ወይም የሚድኑበት ዘር እርሱ መድኃኒታችን ኢሱስ ክርስቶስ የአብርሃም ዘር ከሆነች ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ የሰውን ልጆች በሙሉ በደመ መስቀሉ ባርኮ አንጽቶና ቀድሶ አድኗል፡፡ እግዚአብሔር የምድር አሕዛብ ሁሉ በምሕረትና በይቅርታ እንድንባረክበት የሰጠን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆነ መገንዘብና ማመን ይገባናል፡፡ ይህንን ማወቅ ማስተዋልና ማመን ብፅዕና ማግኘትን ያስከትላል፡፡ ቅድስት ድንግል ማርያም ‹‹ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ነሽ ይሉኛል›› ስትል የተናገረችው ቃለ ትንቢት የእግዚአብሔር ማደሪያ ቤተ መቅደስ መሆኗን ስለተረዳች ነው፡፡ እኛም እንደ እርሷ “አንትሙ ውእቱ ታቦቱ ለመንፈስ ቅዱስ ማለትም እናንተ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ናችሁ” ተብለናል፡፡ ቅድስት ድንግል ማርያም ማኅደረ መለኮት የሆነችው በሃይማኖትና በትሕትና ነው ከዚህ አንፃር እኛም በሃይማኖት ጥላ ሥር ሆነን ንጽሕናችንን ጠብቀን በትሕትና፣ በፍቅር በአንድነት፣ የምንኖር ከሆነ የእግዚአብሔር ማደሪያ

ለመሆናችን ሌላ ምስክር አያስፈልገንም፡፡ ምክንያቱም ጌታችን "ተፋቀሩ በበይናቲክሙ ወእምከመ ተፋቀርክሙ በበይናቲክሙ የአምረክሙ ዓለም በዝንቱ ከመ አርዳእየ አንትሙ፤ እርስ በርሳችሁ አብዝታችሁ ተፋቀሩ፤ እርስ በርሳችሁ ከተዋደዳችሁ ደቀመዛሙርቴ እንደሆናችሁ ዓለም በዚህ ያውቃል" ብሎ እንዳስተማረን ምስክሮቻችን ፍቅር፣ አንድነትና ትሕትና ይሆናሉና ነው፡፡

**የተወደዳችሁ የመንፈስ ቅዱስ ልጆቻችን ምእመናን**

ይህ የምንጾመው የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ጾም ዋና አላማ ከእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የቃል ኪዳኗን በረከት ለማግኘት ነው፡፡ የጾም፣ የጸሎትና የንስሐ ጊዜ ወስኖ እግዚአብሔርን መለመን ከእርሱ ጋር መገናኘት ከጥንት ጀምሮ የሃይማኖት መርሕ ነው፡፡ በዚህ መርሕ ተመርተው ሕዝባቸውንና ሀገራቸውን ከመከራ የታደጉ ቅዱሳን ብዙ ናቸው፡፡ የልቡናቸውን መልካም ምኞት ያገኙትም እንደዚሁ ብዙ ናቸው፡፡ እኛም ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን በደነገገችው የቀኖና ድንጋጌ መሠረት የምንጾመው ጾመ ማርያም ቅዱሳን ሐዋርያት ጌታችን የልቡናቸውን መሻት እንዲፈጽምላቸው የጾሙትና የለመኑትን ያገኙበት ኩነት መነሻ አድርገን እግዚአብሔር እንደነርሱ የልቡናችንን መሻት እንዲፈጽምልን በማመንና ተስፋ በማድረግ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር የቅድስት ድንግል ማርያም ትንሣኤዋንና ዕርገቷን በማሰብ ከእግዚአብሔር ጋር ለመገናኘት ፣ እንጾማለን፣ እንጸልያለን በንስሐም ወደ እርሱ እንቀርባለን፡፡ ቅዱስ ሥጋውን ክቡር ደሙን እንቀበላለን፡፡ በዚህም ከእግዚአብሔር ጋር እንገናኛለን፡፡ ይህ ሲሆን እግዚአብሔር የልቡናችንን መሻት በብሩህ ገጽ ተቀብሎ ይፈጽምልናል፡፡ በአሁኑ ሰዓት የሁላችንም የልቡና መሻት ሀገራችን ኢትዮጵያ ፍጹም ሰላም ያላት ሀገር እንድትሆን ነው፡፡ ይሁንና ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ ሁሉም ነገር ስለማይሆን ፍጹም ሰላም በሀገር ሰፍኖ ሕዝባችን እግዚአብሔር በሰጠው ምድር በፍቅር፣ በአንድነት፣ በነፃነት፣ በእኩልነት እንዲኖር ኦርቶዶክሳውያን ሁሉ በዚህ ወቅት የቅድስት ድንግል ማርያምን ጸሎትና ስእለት ተማኅፅኖና አስተበቍዖት አጋዥ አድርገን በልዩ ሱባዔ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ በንስሐ ፣ በጾም በጸሎት፣ ነዳያንን በመርዳትና ቅዱስ ቁርባንን በመቀበል እርሱን መማጸን ይኖርብናል፡፡

**በመጨረሻም**

በሀገራችን የተከሠቱት ያላስፈላጊ ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት እየተሞከሩ ያሉ አንዳንድ የሰላም ድምጾች ተስፋ ሰጪ ስለሆኑ ሥር ሰደው፤ በተግባር ተተርጉመው ለተጎዳው ሕዝባችን መጠገኛ ይሆን ዘንድ ኦርቶዶክሳውያን ሁሉ በዚህ ዙሪያ በሱባዔው ወቅት ወደ እግዚአብሔር አቤት በማለትና ሂደቱን በመደገፍ የበኩላቸውን ጥረት እንዲያደርጉ መንግሥትም ሆነ የዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ በዚህ በጎ ሐሳብ እንዲገፉበትና ሕዝባችንና ሀገራችንን ከጥፋት እንዲታደጉ አባታዊ መልእክታችንን በእግዚአብሔር ስም እናስተላልፋለን፡፡

እግዚአብሔር አምላክ ጾሙን የሰላም የሥርየት፣ የፍቅር፣ የአንድነት ጾም ያድርግልን፡፡ ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን ይባርክ ወስብሐት ለእግዚአብሔር አሜን፡፡

***አባ ማትያስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ***

***ሊቀ ጳጳስ ዘአኵስም ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት***

***ነሐሴ ፩ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም***

***ዋሽንግተን ዲሲ አሜሪካ***

# ማኅበረ ቅዱሳን ፪ኛውን የግቢ ጉባኤያት ሴሚናር አካሄደ

እንዳለ ደምስስ

ማኅበረ ቅዱሳን ፲፪ኛውን ዓለም አቀፍ የግቢ ጉባኤያት ሴሚናር ከሐምሌ ፳፫-፳፬ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም በሀገር ውስጥ እና በውጭ ሀገራት ከሚገኙ የግቢ ጉባኤያት ተወካዮች በተገኙበት አካሂዷል፡፡ በዚህ ሴሚናር ላይ ከ፪፻፷፪ በላይ በሀገር ውስጥ የሚገኙ የማእከላት አስተባባሪዎችና ተወካዮች እንዲሁም ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ግቢ ጉባኤያት የተውጣጡ ተወካዮች በማኅበረ ቅዱሳን ዋናው ማእከል በመገኘት ሲሳተፉ፤ በውጭ ሀገራት የሚገኙ የግቢ ጉባኤያት ተወካዮች ደግሞ በማኅበራዊ ሚዲያ ቀጥታ ሥርጭት ለመከታተል ችለዋል፡፡

በሴሚናሩ ላይ የተገኙት የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሓፊ እና የኒዮርክ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ የሆኑት ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ባስተላለፉት መልእክት "ትምህርት ለሰው ልጆች የተሰጠ መንፈሳዊ ሀብት ነው" በማለት ትምህርት ለሰው ልጆች የተሰጠ ታላቅ ሀብት መሆኑን አስረግጠው ተናግረዋል፡፡

ብፁዕነታቸው ከዚሁ አያይዘው ስለ ትምህርት አስፈላጊነት ሲያብራሩም "ትምህርት ሥጋዊ ጥበብ ብቻ ሳይሆን መንፈሳዊ ሀብትም ነው፤ እንዲሁም የማያልቅና ፍጻሜም የሌለው ነው" በማለት በጉባኤው ላይ ለተገኙ የግቢ ጉባኤያት ፍሬዎች ገልጸዋል፡፡

በጉባኤው ላይ ዘመኑን የዋጁ በርካታ ጥናታዊ ጽሑፎች ቀርበው ውይይቶችም ተካሂደውባቸዋል፡፡ ከእነዚህም ውስጥ "ማኅበረ ቅዱሳን እና አገልግሎቱ፣ የሕይወት ክህሎት እና ሥራ ፈጠራ፤ የግቢ ጉባኤያት አገልግሎት መልካም ዕድሎችና ፈተናዎች፣ ሚዲያና የግቢ ጉባኤያት ኅትመት ሥርጭት፣ የቤተ ክርስቲያን አንድነትና እና መንፈሳዊ ኅብረት" በሚሉ ርእሶች የቀረቡ ጥናታዊ ጽሑፎች ይጠቀሳሉ፡፡ ከእነዚህ በተጨማሪም "አንድነት እና መንፈሳዊ ኅብረት፣ ቀደምት የማኅበሩ አባላት ተሞክሮና ልምድ" ያካፈሉባቸው መርሐ ግብሮችም ተካሂደዋል፡፡

ማኅበረ ቅዱሳን የግቢ ጉባኤት አገልግሎቱን ለመጀመር ሲነሣ መነሻ ያደረገው ቅድስት ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን በሚገባ የሚያውቅና ከምንጯም መንፈሳዊ ትምህርቷን የቀሰመ፣ በዓለማዊ /አስኳላ/ ትምህርቱም ውጤታማ የሆነና በፈረሰው በኵል እየቆመ ጉድለቶቿን የሚሞላላትን ትውልድ ለመፍጠር ታሳቢ አድርጐ ነው፡፡ ይንንም በሚገባ የተረዳው የቅዱስ ሲኖዶስ ምልአተ ጉባኤም የጉዳዩን አስፈላጊነት በማመን ፈቃድ ሰጥቶት ላለፉት ፴ ዓመታት ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ሲደግፍና አገልግሎቱን ሲፈጽም ቆይቷል ወደፊትም ይቀጥላል፡፡

ማኅበረ ቅዱሳን በአገልግሎት የተጓዘባቸው ዘመናት ሁሉ ቀላልና ምቹ መንገድ እንዳልነበራቸው "ማኅበረ ቅዱሳን እና አገልግሎቱ" በሚል ርእስ በቀረበው ጥናታዊ ጽሑፍ ለማሳየት ተሞክሯል፡፡ በዚህም ጥናታዊ ጽሑፍ ሀገራችን ኢትዮጵያ በምትከተለው ፖለቲካዊ ርእዮተ ዓለም ምክንያት ቤተ ክርስቲያንን ለማዳከም ይደረጉ የነበሩ ሴራዎችና እንቅፋቶች፣ የአፅራረ ቤተ ክርስቲያን መበራከት፣ በራሷ በቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ይንፀባረቁ የነበሩ አሉታዊ አካሄዶች እና ሌሎችም እንቅስቃሴዎች ማኅበሩ የተመሠረተበትን ዓላማ በአግባቡ እንዳያከናውን መሰናክሎች ሆነው ዘልቀዋል፡፡ ነገር ግን እነዚህን መሰናክሎች ለማለፍ በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች የገዳማውያን አባቶች ጸሎት፣ እንዲሁም አገልግሎቱን በቅንነት በሚደግፉ ትጉሃን ኦርቶዶክሳውያን ሁሉ ርብርብ በርካታ መልካም ሥራዎች ተሠርተው አልፈዋል፡፡ አሁንም በጥናትና በዕቅድ ላይ ተመርኩዞ አገልግሎቱን ማጠናከሩን ተገልጿል፡፡

በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ የሚገኙ ኦርቶዶክሳውያን ተማሪዎችን በቅድስት ቤተ ክርስቲያን ለማሰባሰብ በግቢ ግቢ ጉባኤያት ላይ መሥራት አማራጭ የሌለው በመሆኑ እስከ ዛሬ ማኅበሩ የተጓዘባቸውን መንገዶች በመፈተሽና ችግሮችን ነቅሶ በማውጣት በበርካታ አገልግሎታዊ ጉዳዮች ላይ መወያየት ተችሏል፡፡ እያንዳንዱ በመዋቅሩ ውስጥ ያለ አካል ሊያከናውናቸው የሚገቡ ጉዳዮችን መለየትና ተጠያቂነትና ኃላፊነት ያለው አገልግሎት መስጠት በሚቻልበት ሁኔታም ላይ መክሯል፡፡

ብፁዕ አባታችን አቡነ ጴጥሮስ ለጉባኤው ያስተላፉትን መልእክት ስንቃኝም ትምህርት ለሰው ልጆች ሁሉ አስፈላጊና መንፈሳዊ ሀብት ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለደቀ መዝሙሩ ጢሞቴዎስ ስለ ትምህርት አስፈላጊነት ሲያስረዳው "አንተ ግን በተማርህበትና በተረዳህበት ጸንተህ ኑር፤ ከማን እንደተማርኸው ታውቀዋለህና፡፡ ከሕፃንነትህም ጀምሮ ኢየሱስ ክርስቶስን በማመን መዳን የሚገኝበትን ጥበብ ሊሰጡህ የሚችሉትን ቅዱሳት መጻሕፍትን አውቀሃል" በማለት እንደተናገረው እንመለከታለን፡፡ (፪ኛ ጢሞ. ፫፥፲፬)

ቅዱስ ጳውሎስ በዚህ ብቻ አያበቃም፡፡ ለሌላው ደቀ መዝሙሩ ለቲቶ በላከለት መልእክቱ "አንተ ግን ለሕይወት ትምህርት የሚገባውን ተናገር" ሲል ይገልጻል (ቲቶ. ፪፥፩)፡፡ ስለዚህ ትምህርት የተሠወረውን የሚገልጥ ለሰው ልጆች የተሰጠ ታላቅ ሀብት በመሆኑ ኦርቶዶክሳውያን ወጣቶችና የግቢ ጉባኤያት ተማሪዎች ሕይወታቸውን በመንፈሳዊ ትምህርት በማነፅ ሀገርንና ቤተ ክርስቲያንን የመረከብ ግዴታቸውን ለመወጣት መዘጋጀት ይገባቸዋል፡፡ ለዚህም ዝግጅት መንፈሳዊውን ትጥቅ

በማስታጠቅ ረገድ ማኅበረ ቅዱሳን ድርሻው ከፍተኛ ስለሆነ ተናብቦና ተደጋግፎ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የሚፋጠን ትውልድ ማበርከት ይጠበቅበታል፡፡

ይህንን አገልግሎት ጠላት ዲያብሎስ በእያንዳንዱ ርምጃ ለማደናቀፍ የማሰናከያ እንቅፋት ማኖሩ የተለመደ ሲሆን ይህም በመንፈሳውያን የቤተ ክርስቲያን ልጆች ዘንድ በግልጥ የሚታወቅ ነው፡፡ ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት በመዝሙሩ "ከሠወሩብኝ ወጥመድ፣ ዐመፃንም ከሚያደርጉ ሰዎች እንቅፋት ጠብቀኝ" እንዲል (መዝ. ፩፻፵፥፩) መንፈሳዊ ጉዞን ለማደናቀፍ ዲያብሎስ ያዘጋጃቸውን ሰዎች ሴራ በጸሎትና በማስተዋል እያከሸፉ መንዝ ያስፈልጋል፡፡

በተለይም አሁን ባለንበት ዘመን ወጣቱን ትውልድ ከመንፈሳዊ ሕይወት ለመነጠል ፖለቲካዊው ርእዮተ ዓለም ትልቅ መሣሪያ የሆነላቸው ፖለቲከኞች ቤተ ክርስቲያን ላይ በትራቸውን ከመሠንዘር ወደ ኋላ አላሉም፡፡ ሕዝቡን በወንዝ፣ በጐሣ በቋንቋና በዘር በመከፋፈል የሚያራመዱት የሴራ ፖለቲካ ቤተ ክርስቲያንን በእጅጉ እየጐዳት ይገኛል፡፡ እነዚህ አካላት በርካቶችን ከቤተ ክርስቲያን በማስወጣት ዴማሳዊ ጉዞ እንዲጓዙ ብልጭልጩን ዓለም እያሳዩ መልሰው የቤተ ክርስቲያን ጠላቶች እንዲሆኑ መንገዶችን እያመቻቹ ይገኛሉ፡፡ ይህንን መመከት የሚቻለው መንፈሳዊውን ዕውቀት ገንዘብ በማድረግ፤ ማወቅ ብቻም ሳይሆን የተማሩትንም በተግባር በመግለጥ ሊሆን ይገባል፡፡

ለዚህም የግቢ ጉባኤያት ሚና ከፍተኛውን ድርሻ ይወስዳልና ልዩ ክትትልና አፈጻጸም ይጠይቃል፡፡ ኦርቶዶክሳዊ ትውልዱ የሴራ ፖለቲካው ሰለባ እንዳይሆን በአባቶቹ መንገድ መንዝና በማይናወጽ መሠረት ላይ ጸንቶ መቆም አለበት፡፡ ለዚህ ደግሞ አባቶቹ የመረመሩትንና በተግባር የገለጡትን ሕይወት አርአያ በማድረግ በእነርሱ መሠረት ላይ መቆም ይኖርበታል፡፡ ታላቁ የትዕግሥት ሰው ኢዮብ "ዘመናችን በምድር ላይ እንደ ጥላ ነውና፡፡ እኛ የትናንት ብቻ ነን፣ ምንም አናውቅም ስለዚህ የቀደመውን ትውልድ ጠይቅ፣ አባቶቻቸውም ለመረመሩት ነገር ትጋ" በማለት እንደተናገረው በጎውንና ክፉውን መመርመርና ለቀናው መንገድ መሥዋዕትነት መክፈል፣ በሃይማኖትም ጸንቶ መቆም አስፈላጊ ነው፡፡ (ኢዮ.፰፥፰)

ይህንን ፈታኝ የሴራ ፖለቲካ ማዕበል በጽናት ለማለፍ ወጣቱን በተለይም በግቢ ጉባኤያት ውስጥ የሚገኘውን ትውልድ ምቹ ሁኔታዎችን ማለትም ዘመኑ የሚፈልገውን የቴክኖሎጂ አጠቃቀምን በአዎንታዊ ጐን በመጠቀም ወጣቱን ከዘመናዊ ትምህርቱ ባሻገር በመንፈሳዊ ትምህርት እንዲያልፍ በማድረግ ዘመን ከወለዳቸው እኩያት አስተሳሰቦችና ከጥፋት ድርጊቶች ሁሉ መጠበቅ የግቢ ጉባኤያት አገልጋዮች ድርሻ ነው፡፡ ይህንንም ማኅበረ ቅዱሳን የመምራት፣ የመከታተል፣ የማስፈጸም ግዴታውን በተጠናከረ መልኩ ሊንዝበት ይገባል፡፡ ይህንንም ታሳቢ በማድረግ የ፲፪ኛው የግቢ ጉባኤያት ተወካዮች ሴሚናር መዘጋጀቱና መጠነ ሰፊ ምክክር መደረጉ ስሕተቶችን በማረም አገልግሎቱን ካለፉት ዘመናት በተሻለ ሁኔታ ለማስቀጠል፣ ዘመኑን የዋጀ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎትን ለማገልገልም ምቹ የአገልግሎት ዐውዶችን መፍጠር ይችላል፡፡

ሌላው በግቢ ጉባኤያት ውስጥ ጐልተው ከሚታዩትና ለመከፋፈል እንደ ምክንያትነት እየቀረቡ ካሉት ጉዳዮች አንዱ የሆነው የቋንቋ ጉዳይም መፈታት ያለበት ነው፡፡ ለዚህም በተለያዩ ቋንቋዎች ቅዱሳት መጻሕፍትን ማዘጋጀት ማሳተምና ማሠራጨት እንዲሁም በልዩ ልዩ ቋንቋዎች የማስተማር ጸጋ ያላቸውን መምህራንን ማዘጋጀት በወቅቱ ምላሽ የሚፈልጉ መሠረታዊ ፍላጐቶች ናቸው፡፡ ይህንንም ለመፍታት በመላው ሀገሪቱ ውስጥ ያሉ ግቢ ጉባኤያት ትልቅ ሀብት ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ ማስተማር ማሠልጠን፣ ማነጽና ለአገልግሎት ማሰማራት ጊዜው የሚጠይቀው አንገብጋቢ ጉዳይ ነው፡፡ ቋንቋ ኦርቶዶክሳውያንን ለመለያየት ዲያብሎስ ያዘጋጀው ወጥመድ ነውና መንቃት፣ ለጥያቄዎች ፈጣን ምላሽ መስጠትና ትውልዱን ከዘረኝነት ከሃይማኖታዊ ነውጥ መታደግ ተገቢ ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪም በግቢ ጉባኤያት ውስጥ የሚገኘውን የተማረ ኃይል እንዳይባክን መንፈሳዊ አንድነቱን ማጠናከር ላይ በጥንቃቄ መሥራት ያስፈልጋል፡፡ ይህንንም አስመልክቶ "የቤተ ክርስቲያን አንድነትና መንፈሳዊ ኅብረት" በሚል ርእስ በቀረበው ጥናታዊ ጽሑፍ ላይ ኅብረት ለኦርቶዶክሳውያን ከምንጊዜውም በላይ አስፈላጊ መሆኑ ተጠቅሷል፡፡ ጥናቱን ያቀረቡት ዲ/ን ያረጋል አበጋዝ ስለ ኦርቶዶክሳዊ አንድነት ሲገልጹም "ኦርቶዶክሳዊነት ከእግዚአብሔር ጋር ተስማምቶ መኖር ስለሆነ ይህንን መመሪያ መሠረት በማድረግ ኅብረታችንን ማጠንከር፣ ሌሎችንም ወደዚህ ኅብረት እንዲቀላቀሉ ማገዝ ይገባል" በማለት ጠቅሰዋል፡፡ ይህንን ኦርቶዶክሳዊ አንድነትና ኅብረት ለማጠናከርም ግቢ ጉባኤያትን እንደ ምቹ አማራጮች በመጠቀም በሃይማኖቱ የጸና፣ በምግባር የታነፀ አደርጎ መቅረጽ እንዲሚገባ ተጠቅሷል፡፡

በአሁኑ ወቅት የገጠሪቱን ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት እየራቃት ከገጠር ወደ ከተማ እየፈለሰ ያለውን የአብነት (የቆሎ) ተማሪ ባለበት እንዲቆይና ትምህርቱን እንዲከታተል ማድረግ፣ በጐደለው ቦታ ደግሞ በግቢ ጉባኤያት ውስጥ የአብነት ትምህርት መዋቅርን በመዘርጋት፣ መምህራንንም በመመደብና በመደጐም ለክህነት፣ ከዚያም አልፎ ለከፍተኛ የአብነት ትምህርት ማብቃት ጊዜ የሚሰጠው ተግባር አይደለም፡፡

ከዚህ በፊት የነበረውን የግቢ ጉባኤያት የአብነት ትምህርትን ማጠናከር፣ ክትትል ማድረግና ለፍሬ ማብቃት ከማኅበሩ ይጠበቃል፡፡ በየአህጉረ ስብከቱ ያሉ አካላትን የማስተባበር አገልግሎቱንም የመደገፍ እንቅስቃሴ ጤናማ በሆነ መልኩ ማስቀጠል ለነገዋ ቤተ ክርስቲያን ማሰብ ያስፈልጋል፡፡ እስከ አሁን ባለው መረጃ ግቢ ጉባኤያት መምህራንን አዘጋጅተው ተማሪዎችን አስተምረው ለክህነት እያበቁ እንደሚገኙ ቢታወቅም የአህጉረ ስብከቶች ተሳትፎ ግን እጅግ ደካማ ነው ማለት ይቻላል፡፡

አንዳንድ ቦታዎች ላይ በጥሩ ፍቅርና መግባባት እየተሠራ ቢሆንም አብዛኛው ቦታዎች ላይ ግን አገልግሎቱን መደገፍ አለመቻል ራሱን የቻለ ነገር ቢሆንም ለአገልግሎቱ እንቅፋት ሲሆኑ ማየት የተለመደ ነው፡፡ እነዚህን ችግሮች ለማቃለልና ለመፍታት ከብፁዓን አበው ሊቃነ ጳጳሳት አንሥቶ እስከ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ድረስ ባለው መዋቅር ጥረት ማድረግ ይጠይቃል፡፡ ለዚህም ለተፈጻሚነቱ ቀን ከሌሊት መሥራት አዳዲስ ዕቅዶችን በመንደፍ አሳማኝ ሥራዎችን ሠርቶ ማሳየት ይገባል፡፡ በተለይም ከላይ እንዳነሣነው በቋንቋና ከቋንቋ ጋር በሚነሡ እንቅፋቶች ላይ ትኩረት በማድረግ መሥራት ያስፈልጋል፡፡

የዘር ፖለቲካው ከሚፈጥራቸው አሉታዊ ተጽዕኖዎች ማዶ አሻግሮ መመልከትና ሊመጡ የሚችሉትን ፈተናዎች ቅድሚያ ታሳቢ ያደረገ አገልግሎትን ማገልገልና ለችግሮቹ ከወዲሁ መፍትሔ መስጠት ይገባል፡፡ ፈተናዎችን እየተከተሉ ለማጥፋት ከመሯሯጥ ይልቅ በቅድሚያ ሊመጣ ያለውን ፈተና በመለየት ማለፊያ መንገዶችን ማዘጋጀት የመፍትሔ አካል መሆን ያስችላል፡፡ ይህም ሊመጣ ያለውን አደጋ ይቀንሰዋል፡፡ ስለዚህ ተለዋዋጭ የሆነውን የፖለቲካ ወረርሽኝን ለመቋቋም ቤተ ክርስቲያንን የሚያውቅ፤ የሚረዳ፣ የተማረና ለአገልግሎት ራሱን ያዘጋጀ አገልጋይና ተገልጋይ መፍጠር የቤተ ክርስቲያን ኃላፊነት ቢሆንም በየመዋቅሩ ያሉትን አገልጋዮች ከግል ጥቅም ይልቅ ሀገርንና ቤተ ክርስቲያንን እንዲያስቀድሙ፣ ለተጠሩበት ዓላማም ታማኝ ሆነው እንዲገኙ መሥራት ጊዜው የሚጠይቀው አንገብጋቢ ጉዳይ ነው፡፡ በየጊዜው ሥልጠናዎችን መሥጠት፣ ዘመኑን መረዳትና ይህንንም መቋቋም የሚችል አገልጋይ ማፍራት፣ ራሱንም የመፍትሔ አካል አድርጐ ለሌሎች ምሳሌ በመሆን ሠርቶ የሚያሠራ አድርጐ መቅረጽ ያስፈልጋል፡፡

መማር ብቻውን መንፈሳዊ አያሰኝምና በተግባር ማሳየትና መግለጥ የቀደሙ አባቶችን ተጋድሎ መመሪያ አድርጐ መጓዝ፣ ለፈተና ከመንበርከክ ፈተናውን በጥበብ የማለፍን ትዕግሥት መጐናጸፍ ይገባል፡፡ ቅዱስ ዮሐንስ በራእዩ "ትቀበለውም ዘንድ ስላለህ መከራ ምንም አትፍራ፤ እነሆ እንድትፈተኑ ሰይጣን ከእናንተ አንዳንዶችን ወደ እሥር ቤት እንዲገቡ ያደርጋል፤ ዐሥር ቀንም መከራ ትቀበላላችሁ፤ እስከ ሞት ድረስም የታመንህ ሁን የሕይወት አክሊልንም እሰጥሃለሁ" በማለት እንደነገረን መጽናት ተገቢ ነው፡፡ (ራዕ.2.0)

ከማኅፀነ ዮርዳኖስ ከአብራከ መንፈስ ቅዱስ በጥምቀት ተወልደን በክርስቶስ ክርስቲያን ተብለናልና የተጠራንበትን ዓላማ ዘንግተን የዘርና የብሔር ልጓም ስቦን ወንዝንና ቋንቋን ተገን አድርገን እንድንጓዝ ዲያብሎስ ወጥመዱን ዘርግቷልና ልናውቅበትና መንፈሳዊውን የዕቃ ጦር ታጥቀን ልንመክተው ይገባል፡፡ በነፈሰበት ከመንፈስ፣ በትንሹም በትልቁም ከመደናገጥና መውጫ መግቢያ ከማጣት በትምህርትና በዕውቀት የታነፀ፣ በሃይማኖት የቆመ ትውልድ ሆነን ቤተ ክርስቲያንና ራሳችንን ለመታደግ ቆርጠን መነሣት ያስፈልጋል፡፡ ለዚህም መማር፣ ማወቅ፣ መመራመር ቅዱሳን አባቻችን የተጓዙበትን መንገድ መከተል ይጠበቅብናል፡፡

ትምህርት ለተጠቀመበት መንፈሳዊ ሀብት ነው፡፡ የግቢ ጉባኤያት ተማሪዎችም መንፈሳዊውን ዕውቀት ለመቅሰም በትክክለኛው ዕድሜና በትክክለኛ ቦታ ላይ የተገኙ ወጣቶች ናቸው፡፡ እነዚህን ወጣቶች ጥላቻን፣ መከፋፈልንና ዘረኝነትን በመስበክ ለሀገርም ሆነ ለቤተ ክርስቲያን ጠላቶች ሆነው የተጣመመ ዛፍ ሆነው እንዳያድጉ መንፈሳዊውን ዕውቀት ማስታጠቅ ያስፈልጋል፡፡ ትውልድን መታደግ የቅድስት ቤተ ክርስቲያን ልጆች የሆንን ሁሉ ላይ የተጣለ ኃላፊነት ነው፡፡ ለእከሌ የተሰጠ የአገልግሎት ዘርፍ ነው በሚል ነገሮች ሲበላሹና ቤተ ክርስቲያን ስትቃጠል ከዳር ቆመን እሳት መሞቅ ተገቢ አይደለም፡፡ የተጠሩበትንም ዓላማ መካድ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ወደ ሞት ይመራልና ትውልዱን ለመታደግ እንነሣ፡፡ ማኅበረ ቅዱሳን ብቻ ነው ይህንን የሚሠራው በሚል ጀርባ መስጠት ከመጠየቅ አያድነንም፤ አላስፈላጊ ወቀሳንም ትተን ቤተ ክርስቲያንን ታሳቢ ያደረገ የጋራ አገልግሎት በአንድነት መፈጸም ነው ትልቁ መፍትሔ፡፡

ማኅበረ ቅዱሳን የአባቶች አደራ በታማኝነት ተቀብሏልና እንደዚህ ቀደሙ ለማገልገል፣ ደካማ ጐኑን በማረም፣ በመመካከርና በፍቅር ለማገልገል ሀገርና ቤተክርስቲያን ተረካቢ ትውልድ ላይ መሥራቱ ይቀጥላል፡፡ ነገር ግን ለዚህ አገልግሎቱ ድጋፍ ይሻል፡፡ ቢቻል ቀና ትብብር ማድረግ ከመንግሥት አካላት፣ እንዲሁም ከሀገረ ስብከት እስከ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ድረስ ነገን ታሳቢ ያደረገ አገልግሎት ለመፈጸም እንቅፋቱን ለማስወገድ ትብብር ሊያደርጉ ይገባል፡፡ የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊ እና የኒውዮርክ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አባታችን አቡነ ጴጥሮስ "ትምህርት ለሰው ልጆች ሁሉ የተሰጠ ሀብት ነው፡፡" በማለት አባታዊ ምክራቸውን እንዳስተላለፉልን ለእኛም ሆነ ለሀገር በማይጠቅም ይልቁንም እርስ በእርስ በምንጠፋፋበት በሴራ ፖለቲካ ትብትብ ተተብትበን በዘርና በቋንቋ ከምንባላ ይልቅ ለሥጋዊም ሆነ ለመንፈሳዊው ሕይወታችን እንዲሁም ለቤተሰቦቻችን ለቅድስት ቤተ ክርስቲያንችንና ለሀገራችን በእጅጉ በሚጠቅመን ሀብታችን በትምህርታችን ላይ ውጤታማ ለመሆን በሰከነና በተረጋጋ መንፈስበመካከላችን ያሉ ከፋፋይ ልዩነቶችን አስወግደን በጋራ መቆም ይጠበቅብናል፡፡ የሴሚናሩ ተሣታፊዎችም በየተወከሉበት ሆነው ሊመጣ ያለውን አደጋ ለመመከት ከፊት ይልቅ መትጋት እንደሚገባቸው በማመን ለአገልግሎት ተሰማርተዋል፡፡

ማኅበረ ቅዱሳን በሀገር ውስጥ ፶ ማእከላትና ፬፻፵፬ ወረዳ ማእከላት እንዲሁም ፩፻፲፬ ግንኙነት ጣቢያዎች ያሉት ሲሆን በውጭ ሀገራት ደግሞ ፮ ማእከላትና ፳፮ ግንኙት ጣቢያዎች አሉት፡፡ በግቢ ጉባኤያት ደረጃ በሀገር ውስጥ ፬፻፳፯ ግቢ ጉባኤያት እንዲሁም በውጭ ሀገራት ፲፮ ግቢ ጉባኤያትን በማቋቋም ቅድስት ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ከ፲፱፻፹፬ ዓ.ም ጀምሮ በማገልገል ላይ ይገኛል፡፡ በዚህም አገልግሎቱ ከ ፯ መቶ ሺህ በላይ ቤተ ክርስቱያንን የሚያውቅና የሚረዳ፣ ለአገልግሎትም የሚፋጠን ትውልድ ማፍራት ችሏል፡፡

# ዘመናቸውን ሁሉ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የሰጡ እውነተኛ አባት

ካሳሁን ለምለሙ

**ክፍል ሁለት**

***የተወደደዳችሁ አንባብያን የዚህን ጽሑፍ የመጀመሪያ ክፍል ከዚህ በፊት በነበረው እትም ላይ ማቅረባችን ይታወሳል። ሁለተኛውንና የመጨረሻውን ክፍል ደግሞ እነሆ፦***



መጋቤ ምሥጢር ዶ/ር ኀሩይ ኤርምያስ

**ስምዐ ጽድቅ፦ መንፈሳዊ አገልግሎትን የት ጀመሩ?**

**መጋቤ ምስጢር ዶክተር ኀሩይ፦** መጀመሪያ መንፈሳዊ አገልግሎት የጀመርኩት በእቲሳ ደብረ ጽላልሽ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ገዳም የቅኔ መምህር ሆኜ ነው። ለአንድ ዓመት ከስድስት ወር በገዳሙ በቅኔ መምህርነት ሳገለግል ከቆየሁ በኋላ አዲስ አበባ ወይብላ ኢሰያ ደብረ መለኮት ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን በዋና ጸሐፊነት ተመድቤ አገልግያለሁ። ከጸሐፊነት ድርሻዬ በተጨማሪ ሌሎች ተያያዥነት ያላቸው አገልግሎቶችን እፈጽም ነበር። አዲስ አበባ ሀገረ ስብከት በሚገኙ ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት እንዲሁ ተዘዋውሬ ለተወሰኑ ዓመታት በተለያዩ የአገልግሎት ዘርፎችና በተለያዩ ኃላፊነቶች አገልግያለሁ።

ሀገር ቤት እግዚአብሔር በፈቀደልኝ መጠን እያገለገልኩ በነበረበት ወቅት አውሮፓ ሆላንድ ውስጥ አዲስ የተሠራ አጥቢያ ላይ የሚያገለግሉ ወንድሞችና አባቶች ባቀረቡልኝ የአገልግሎት ግብዣ መሠረት ወደ ሆላንድ ለማቅናት ዝግጅት እያደረኩ በነበረኩበት ወቅት የጋበዙኝ አካላት ከአዲስ አበባ ቀጥታ ሆላንድ ሳይሆን በጀርመን አድርጌ እንደምሄድ ነገሩኝ። እኔም በተነገረኝ መረጃ መሠረት ጉዞዬን ቀጥታ ከኢትዮጵያ ወደ ጀርመን አደርኩ። ከዚያም እኔ ለሀገሩ ባዳ በመሆኔና የጉዞ ፕሮግራሙ የእኔ ባለመሆኑ እዚያ ሁኜ የእነርሱን ትእዛዝ መጠበቅ ጀምርኩ። ከጥቂት ወራት በኋላ ደውለው ሆላንድ ውስጥ ችግር እንዳለና ጀርመን ውስጥ መቆየት እንዳለብኝ ስለነገሩኝ ለተወሰነ ጊዜ እዚያው ለመቆየት ወሰንኩ። እኔ ግን ከሀገር ውጭ ለማገልገል ፍላጎት ባይኖረኝም አዲስ የተሠራው ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን በቂ አገልጋይ እንደሌለው ስለተነገረኝ የአገልጋይ እጥረት ችግሩን በመጠኑም ቢሆን የማቃልል መስሎኝ ነው ወደዚያ ያቀናሁት። ነገር ግን ጊዜው እየገፋ ሲሄድ ለጀርመን መንግሥት በጥገኝነት እጀን ሰጠሁ።

ጀርመን ሀገር በጥገኝነት ለስምንት ወራት በካምፕ ውስጥ ከቆየሁ በኋላ እዚያ መኖሬን ያወቁ ወንድምና እህቶች የማገለግልበትን ቤተ ክርስቲያን ፈለገው አገኙልኝ። ከዚያም እየተመላለስኩ አገለገልኩ። ከካምፑ ከወጣሁ በኋላም የካስል ደብረ ቀራንዮ መድኃኔዓለም የሚባል ደብር ላይ በአስተዳደሪነት ተመድቤ ማገልገል ጀመርኩ። ለረጅም ጊዜ ተዘግታ የነበረችውን ዳርምሽታታ ሐመረ ኖኅ ቅድስት ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያንንም ደርቤ ለተወሰኑ ዓመታት አገልግያለሁ። ሁለቱን አጥቢያዎች በዋና አስተዳደሪነት እያገለገልኩ በነበርኩበት ወቅት የጀርመን ሀገረ ስብከት ምክትል ሥራ አስኪያጅ ሆኜ ተመድቤ አምስት ዓመታት ያህል አገልግያለሁ። ከዚያ በኋላ ከቦታው ርቀት፣ ጀርመን ሀንቡርግ ከተማ እየተከታተልኩት ካለው ትምህርትና ከአግልግሎት ጫና የተነሣ ደርቤ አስተዳድራት የነበረችውን ዳርምሽታታ ሐመረ ኖኅ ቅድስት ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያንና የሀገረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጅነት ኃላፊነቴን ለሌሎች አገልጋዮች ሰጥቼ በአሁኑ ወቅት ሀንቡርግ ከተማ

በቅርብ ርቀት የሚገኙ ሁለት አጥቢያዎችን ደርቤ በማስተዳደር ላይ እገኛለሁ፡፡

**ስምዐ ጽድቅ፡- በውጭው ዓለም ያለውን የቤተ ክርስቲያን የአገልግሎት ምን እንደሚመስል ቢገልጹልኝ?**

**መጋቤ ምስጢር ዶክተር ኀሩይ፡-** የቤተ ክርስቲያን አስተምህሮዋንና ማንነቷን አጠቃላይም ሀገርን በነጻነት ለማስተዋወቅ በውጭው ዓለም መልካም እድል ተፈጥሮላታል፡፡ በዚህ ረገድ በውጭ ዜጎች ዘንድ ያላት ተቀባይነትና ዕውቅና ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መጥቷል፡፡ በጋብቻና በተለያዩ ሁኔታዎች ወደ እናት ቤተ ክርስቲያን የሚመጡ የውጭ ሀገር ዜጎችን አሳምኖ በማስተማር የሥላሴ ልጅነትን እንዲያገኙ የማድረጉ እድል በጣም ሰፊና እየተሠራበት ያለ አካሄድ ነው፡፡ የምእመናንን ወደ ውጭ ሀገር መሰደድ ተከትሎ ካህናት ምእመናን ለማገልገል መሰደዳቸው በውጭው ዓለም የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት እንዲሰፋና አስተምህሮዋ በደንብ እንዲታወቅ አግዟል፡፡ ለአብነትም ጀርመን ላይ ብቻ ፳፪ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት ይገኛሉ፡፡ እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት በራሳቸው ሀገርን ከማስተዋወቅና የሀገርን ገጽታ በመገንባት ረገድ የአምባሳደርነት ሚና ሲኖራቸው ከፍ ሲልም እንደ ኢምባሲ ሊያገለግሉ ይችላሉ፡፡

በቤተ ክርስቲያናችን ከሚሰበከው የክርስቶስ ወንጌል በተጨማሪ የኢትዮጵያን ባህል፣ ቋንቋ፣ታሪክ፣ ትውፊትና ሌሎች ሀገራዊ ምልክቶችን ለማስተዋወቅ ከእርሷ በላይ ቅርብ የሆነ አካል አይኖርም፡፡ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የሌለችበት የዓለም ክፍል ባለመኖሩ ቅዳሴዋንና ውዳሴዋን እንዲሁም አጠቃላይ ሃማኖታዊ ትውፊቷን ለማየትና ለምርምር ተግባር ከተለያዩ አካባቢዎች የሚመጡ የውጭ ሀገር ዜጎች አሉ፡፡ ይሁን እንጂ በውጭ ሀገር ያለችው ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት አልጋ በአልጋ የሆነ አይደለም፡፡ ይህም ሲባል አብዛኛውን ጊዜ በውጭ ሀገራት ያሉ አብያተ ክርስቲያናት የሚቋቋሙት አነስተኛ ቍጥር ባላቸው የጽዋ ማኅበራት አማካይነት ነው፡፡ ከምእመናን የቍጥር ማነስና ከገንዘብ አቅም ችግር የተነሣ አብዛኛውን ጊዜ አብያተ ክርስቲያናቱ የራሳቸው የሆነ ሕንጻና በቂ ካህናት አገልጋዮች የሌላቸው በመሆኑ አንድንድ ጊዜ አገልግሎቱ የታሰበውን ያህል ርቀት መጓዝ አይችም፡፡ ይህም ሆኖ ግን በአሁኑ ሰዓት በአገልጋዮችና በምእመናን ብርቱ ጥረት አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት የራሳቸው የሆነ ሕንጻ ቤተ መቅደስ እየገዙና የጎደሉ አገልጋዮችን እያሟሉ ይገኛሉ፡፡ አንዳንድ ጊዜም ምእመናን ያለ ምንም በቂ ምክንያት ከቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የመራቅ ሁኔታ ሲከሰት ተበታትነው ከመኖራቸው የተነሣ ፈልጎ ለመጠየቅና የኀዘናቸውና የችግራቸው ተካፋይ ለመሆን እንቸገራለን፡፡ በተቻለ መጠን ምእመናን ከአገልግሎት እንዳይርቁና እንዲጽናኑ የማድረግ ሥራዎችን እየሠራን እንገኛለን፡፡

እኛ አገልጋዮች በትዕግሥትና ምእመናን በደስታና በፍቅር መያዝ ከቻልን የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት ከነበረው አንድና ሁለት ርምጃ ማስኬድ እንችላለን፡፡ አገልጋዮች ከቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ውጭ የተለያየ አይነት የፖለቲካ አመለካከት ልዩነት ቢኖራቸውም እንኳን በምእመናንና በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ላይ እንዲያንጸባርቁ አንፈቅድም፡፡

በተለያየ የፖለቲካ አመለካከት የተራራቁ ምእመናንን ቤተ ክርስቲያን ያስታረቂነት ሚናዋን በመወጣት ሐዋርያት በሠሯት አንዲት ቤተ ክርስቲያን ሥር ሆነው መንግሥቱን እንዲወርሱ የማድረግ ሥራ ስንሠራ ቆይተናል፡፡

**ስምዐ ጽድቅ፡- በውጭ ዓለም ለበርካታ ዓመታት ቤተ ክርስቲያንን ያለ ደሞዝ ሲያገለግሉ ቆይተዋልና በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሆነው ለማገልገል ምን አነሣሣዎት?**

**መጋቤ ምስጢር ዶክተር ኀሩይ፡-** ቤተ ክርስቲያንን ያለ ወርኃዊ ደሞዝ ለማገልገል ስወስን የተለየ የገንዘብ አቅም ኖሮኝ አልነበረም፡፡ ይልቁንስ አንዳንድ አጥቢያዎች አይደለም ለአገልጋይ ካህናት የሚከፍሉት ወርኃዊ ደሞዝ ሊኖራቸው ይቅርና ለውዳሴ ቅዳሴ የሚያገለግሉ ንዋያተ ቅድሳትን ለማሟላት በጣም የሚቸገሩ ናቸው፡፡ እኔም በአስተዳዳሪነት ተመድቤ አገለግልበት የነበረው የጀርመኑ ካስል ደብረ ቀራንዮ መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ የሆነ የገንዝብና አገልጋይ እጥረት የነበረበት ነው፡፡ ታዲያ በዚህ ሁኔታ ውስጥ ያለን ቤተ ክርስቲያን በወርኃዊ ደሞዝ ማገልገል ጊዜያዊ ሥጋዊ ፍላጎትን ያሟላ እንደሆነ እንጅ ሰማያዊ በረከትን አያስገኝም፡፡ ይህ ቤተ ክርስቲያን ባለበት ችግር ምክንያት ለመዘጋት እጅግ የቀረበ ስለነበር በዚያን ጊዜ ከቤተ ክርስቲያኑ

ደሞዝ ማግኘት ሳይሆን የታየኝ የጽዋ ማኅበራትንና አገልግሎቱን ማጠናከር ነበር፡፡ ቤተ ክርስቲያኑ በገንዘብና በአገልግሎት ከተጠናከረበት ጊዜ ጀምሮ ግን ወርኃዊ ደሞዝ እየተከፈለኝ እስካሁን በአገልግሎት ላይ እገኛለሁ፡፡

**ስምዐ ጽድቅ፡- በቀጣይ በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ላይ ምን አይነት አሻራ አኑረው ማለፍ ይፈልጋሉ?**

***መጋቤ ምስጢር ዶክተር ኀሩይ፡-*** እስካሁን ድረስ የሚጠበቅብኝን ያህል ቤተ ክርስቲያንን ማገልገሌን እርግጠኛ ባልሆንም ከዚህ በኋላ ግን ሙሉ ዘመኔን ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት እሰጣለሁ ብዬ አምናለሁ፡፡ ማገልገል እየቻልኩ ጊዜዬን ያለ አገልግሎት ማሳለፍ አልፈልግም፡፡ በአገልግሎትና በትምህርት ያገኘሁትን መንፈሳዊና ዓለማዊ ዕውቀት ለቤተ ክርስቲያንና ለምእመናን በሚጠቅም ሁኔታ እጠቀምበታለሁ የሚል እቅድ አለኝ፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ አብያተ ክርስቲያናት የራሳቸው የሆነ ሕንጻ እንዲኖራቸው የጀመረኩትን ጥረት መቀጠልና በመሠራት ላይ ያሉ ሁለት የቤተ ክርስቲያን አብያተ መጻሕፍትም ተጠናቀው ለአገልግሎት እንዲበቁ ማድረግ ነው፡፡ አብያተ መጽሐፍቶቹም የተሟላ ዘመናዊ አገልግሎት እንዲሰጡ የበኩሌን አደርጋለሁ፡፡ ከላይ የጠቀስኳቸው በሂደት ላይ ያሉ ሲሆኑ ቀጣይ ላከናውናቸው ያሰብኳቸው በርካታ ዕቅዶችም አሉኝ፡፡ እግዚአብሔር ቢረዳኝና በሕይወት ብቆይ ዕቅዶቸን አንድ በአንድ እፈጽማቸዋለሁ ብዬ አስባለሁ፡፡ ቤተ ክርስቲያን የምትጠብቅብኝን ለመስጠትና ጊዜዬንና ጉልበቴን ለማበርከት ሙሉ ፈቃደኛ ነኝ፡፡

**ስምዐ ጽድቅ፡- ለእርስዎ እዚህ ደርጃ መድረስ የተለየ ድርሻ ነበራቸው የሚሏቸው ሰዎች ካሉ የነበራቸው ድርሻ ምን እንደነበረ ቢገልጹልን?**

***መጋቤ ምስጢር ዶክተር ኀሩይ፡-*** በመጀመሪያ ደረጃ የእኔን ፍላጎት ለመሙላት ብዙ የደከመችው ወላጅ እናቴ ወይዘሮ አልማዝ አለሙ ሲሆኑ በመቀጠልም ሌሎች ቤተሰቦቼና አመስግኝ የማልጨርሳቸው የመንፈሳዊና የዘመናዊ ትምህርትን ያስተማሩኝ መምህራን በሕይወቴ ላይ ከፍተኛ ድርሻ ነበራቸው፡፡ በተለይ በቅኔ ቤት ቆይታዬ ጊዜ አንድም ቀን ለልመና ሳልወጣ ለብዙ ወራት ቁራሽ ለምነው ያበሉኝና እንደወንድም የተንከባከቡኝ መጋቤ ምስጢር አባ ኢያሱ ገብረ አሌፍ (የምስካየ ኅዙናን መድኃኔዓለም ገዳም የቅኔ መምህር) ምስጋና ላቀርብላቸው እወዳለሁ፡፡ አሁን በሕይወተ ሥጋ የሌሉት መጋቤ ሥርዓት ዮሐንስ ዋለ ንባብና የቁጥር ትምህርት ስማር መምህሬ ከሥርክ አገልግሎት ነፃ ሆነው እንዲያስተምሩኝ በመፍቀድ ከፍተኛ እገዛ አድርገውልኛል፡፡ ከዚያም የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ዋና ጸሐፊ በነበሩበት ወቅት የወይብላ ቅድስት ድንግል ማርያም ቤተ ክርስቲያን ጸሐፊ ሆኜ እንድመደብ አድርገዋል፡፡ ይህንን ሁሉ ያደረጉልኝ ያለምንም ምክንያት በደግነት ስለሆነ የማልረሳቸው ባለውለታዬ ናቸው፡፡ ከእርሳቸው በተጨማሪ ስማቸውን ያላነሳኋቸው በአገልግሎቴና በትምህርቴ ከፍተኛ እገዛ ያደረጉልኝ በርካቶች ናቸው፡፡

**ስምዐ ጽድቅ፡- በመጨረሻ ቀረ የሚሉት ነገር ካለ ቢጨምሩልን?**

***መጋቤ ምስጢር ዶክተር ኀሩይ፡-*** ቤተ ክርስቲያናችን ያላትን ጥንካሬና ሃይማኖታዊ ዕሴት ይዛ እንድትቀጥል በሀገርና በውጭ ሀገር ያለን ምእመናንና አገልጋዮች ከመቼውም ጊዜ የተሻለ ሥራ መሥራት ይጠበቅብናል፡፡ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ያለንን ጊዜና ጉልበት ሁሉ መስጠት አለብን፡፡ በተለይ በንዋይም ሆነ በዕውቀት ማነስ ተታለው የጠፉ ወገኖችን አስተምሮ በመመለስ ወደ እግዚአብሔር እንዲቀርቡ የማድረግ ትልቅ ኃላፊነት አለብን፡፡

ዘመኑ የወለደውን ቴክኖሎጂና በየሀገራቱ ያለውን የዕምነት ነጻነት በመጠቀም ኢትዮጵያውያንን ብቻ ሳይሆን የሌላ ሀገር ዜጎችንም በስብከተ ወንጌል መድረስ ያስፈልጋል፡፡ በተለይ የሌላ ሀገር ዜጎችን በቋንቋቸው በማስተማር ወደ ቤተ ክርስቲያን ማቅረብ ቢቻል የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት ዓለም አቀፋዊ ለማድረግና ለማስፋት ያግዛል፡፡

በተጨማሪም በውስጣችን (በአገልጋዮች) መካከል ያለውን አለመግባባት ፍጹም መንፈሳዊ በሆነ ጥበብ በመፍታት ቤተ ክርስቲያን አሁን እየገጠማት ያለውን ችግር ሳይሆን ወደፊት ሊገጥማት የሚችለውን የከፋ ችግር በማሳብ ለመፍትሔውም በአንድነት መሥራት ያዋጣል እላለሁ፡፡

# መንግሥት ቤተ ክርስቲያን የምታከናውናቸውን የልማት ሥራዎች ከመንቀፍ ይልቅ ቢደግፍ መልካም ነው!

ካሣሁን ለምለሙ

*በአዲስ አበባ ሀገር ስብከት በየካ ወረዳ ቤተ ክህነት ሥር የምትገኘው ደብረ ዕንቊ ልደታ ለማርያም ቤተ ክርስቲያን በ፲፱፻፹፮ ዓ.ም የተመሠረተች ሲሆን ከተመሠረተችበት ጊዜ ጀምሮ ያልተቋረጠ መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎት ስትሰጥ ቆይታለች፡፡ እጅግ ሊለማ የሚችል የብዙ ጋሻ መሬት ባለቤት የሆነችው ይህች ቤተ ክርስቲያን ከዚህ ቀደም ባላት የመልማት ልክ  እንዳለማች ቦታው ድረስ ተገኝቶ ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ ሰፊ የሆነ ሕጋዊ የመሬት ይዞታ ያላት ደብረ ዕንቊ ልደታ ለማርያም ቤተ ክርስቲያን ባላት ሀብት ልክ ያለመልማቷ ቁጭት ውስጥ የከተታቸው የቤተ ክርስቲያኗ አገልጋዮችና ምእመናን የልማት ተጠቃሚ እንድትሆን ከፍተኛ እንቅስቃሴ ካደርጉ ዓመታትን አስቆጥረዋል፡፡*

*ስለሆነም ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ከዚህ ቀደም የነበረውን ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን በአዲስ ለመቀየር እጅግ ግዙፍና ዘመኑን የዋጀ ሕንጻ ቤተ መቅድስ ተገንብቶ ወደ መጠናቀቅ ደርጃ ደርሷል፡፡ ከሕንጻ ቤተ ክርስቲያኑ ግንባታ ጎን ለጎን የቤተ ክርስቲያኑን ይዞታ የሚመጥኑ የተለያዩ ፕሮጀክቶችን ተግባራዊ ለማድረግ ከሀገር ውስጥ እስከ ውጭ ሀገራት ከፍተኛ እንቅስቃሴ እየተደረገ ይገኛል፡፡ ከእነዚህ ፕሮጀክቶች መካከል የቅዱስ መስቀል ፕሮጀክት ሥራ በአብነት ይጠቀሳል፡፡ ይህ የመስቀል ፕሮጀክት በውስጡ የተለያዩ ንዑስ ፕሮጀክቶች ሲኖሩት  ለቤተ ክርስቲያንና ለሀገር ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖራቸዋል ተብሎ ይታመናል፡፡*

*ከእነዚህ ፕሮጀክቶች መካከል የሱባኤ መያዣ ቤቶች፣ የጥናትና ምርምር ማእከል፣የሱስና ልማዶች ማገገሚያ ማእከል፣ግልጽ የማንበቢያ ቦታ፣አዕምሮን የሚያድስ መካነ ሐመልማል እንዲሁም ሌሎች ይገኙበታል፡፡ እንደነዚህ አይነት ግዙፍ መሠረተ ልማቶች የሚበረታቱ ሆነው ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ከእነዚህ ልምድና ተሞክሮ በመውሰድ ቤተ ክርስቲያን፣ምእመናን ከፍ ሲልም ሀገር የምትጠቀምበትን ምቹ ሁኔታ መፍጠር ተገቢ እንደሆነ በማመን በየካ ደብረ ዕንቊ ልደታ ለማርያም ቤተ ክርስቲያን ያለውን መንፈሳዊ አገልግሎትና በፕሮጀክቱ ትግበራና አፈጻጸም ዙሪያ የደብሩ ዋና አስተዳደሪ ከሆኑት መልአከ ሰላም ነብዩ ልዑል ጌጡ ጋር አጭር ቆይታ አድረገናል፡፡ መልካም ንባብ፡፡*

**ስምዐ ጽድቅ፡- በየካ ደብረ ዕንቊ ልደታ ለማርያም ቤተ ክርስቲያን ያለው መንፈሳዊ አገልግሎት ምን እንደሚመስል ቢገልጹልን?**

**መልአከ ሰላም ነቢየ ልዑል ጌጡ፡-** በየካ ደብረ ዕንቊ ልደታ ለማርያም ቤተ ክርስቲያን ሁልጊዜ ያልተቋረጠና ከዚህ ቀደም ከነበረው እጅግ የተሻለ መንፈሳዊ አገልግሎት እየተሰጠ ይገኛል፡፡ ካህናት፣ሰበካ ጉባኤውና ምእመናን በቅንጅትና በትብብር የሚያገለግሉባትም ደብር ናት፡፡ በደብሩ ፳ ካህናት፣ ፲፪ ዲያቆናት፣ ፲፩ ሰባክያነ ወንጌልንና ድጋፍ ሰጪ አገልጋዮችን ጨምሮ በአጠቃላይ ሃምሳ ስድስት ያህል አገልጋዮች ይገኛሉ፡፡ የደብሩ ሰንበት ትምህርት ቤትም የተደራጀና የተጠናከረ ሲሆን አብነት ትምህርት ቤት ለማቋቋምም በእንቅስቃሴ ላይ እንገኛለን፡፡



**መልአከ ሰላም ነቢየ ልዑል ጌጡ**
**የደብረ ዕንቊ ልደታ ለማርያም ቤተ ክርስቲያን ዋና አስተዳዳሪ**

**ስምዐ ጽድቅ፡- በደብረ ዕንቊ ልደታ ለማርያም ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ አገልግሎት ላይ ያሉ ተግዳሮቶች ምንድናቸው?**

**መልአከ ሰላም ነቢየ ልዑል፡-** ደብረ ዕንቊ ልደታ ለማርያም ቤተ ክርስቲያን በአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት በየካ ወረዳ ቤተ ክህነት ሥር የምትገኝ ትሁን እንጂ ያለችበት ቦታ ከመሐል ከተማ ወጣ ባለ ተራራማ አካባቢ ነው፡፡ ይህ

በመሆኑም ከዓመታዊና ወርኃዊ የንግሥ በዓል በስተቀር ምእመናን በብዛት በየቀኑ የሚመጡባት ደብር አይደለችም፡፡ በዚህም የተነሳ ቤተ ክርስቲያኗ ከልጆቿ ማግኘት ያለባትን ድጋፍ ሳታገኝ በመቅረቷ የአገልጋይ ካህናትን ወርኃዊ ደሞዝ መሸፈን እንዳትችልና መንፈሳዊ አገልግሎቱንም ወደ ተሻለ ደረጃ ከፍ ለማድረግ እየተቸገረች ትገኛለች፡፡ ይሁን እንጅ ከአገልጋዮችና ከአካባቢው ምእመናን ጋር በመነጋገር የስብከተ ወንጌል አገልግሎት በስፋት በመስጠት በየዕለቱ የምእመናንን ቁጥር ለማሳደግ ሥራዎች እየተሰሩ ይገኛሉ፤ለወደፊትም የተጠናከረ ሥራዎች ይሰራሉ ብለን እናምናለን፡፡ የምእመናንን ቁጥር ከመጨመር አንጻር እስካሁን በሠራናቸው ሥራዎች ተጨባጭ ለውጥ ማምጣታችንን መረዳት ችለናል፡፡

እስካሁን ድረስ ከሙዳየ ምጽዋትና ከቀብር ቦታ ከሚገኝ ገቢ ውጭ ቤተ ክርስቲያኗ እንደሌሎች አድባራት ተጨማሪ ገቢ የላትም፡፡ ቤተ ክርስቲያኗ ያላትን የመሬትና ሌሎች ጸጋዎችን አሟጣ ባለመጠቀሟ አገልግሎቷን ሊደግፍ የሚችል በቂ ገቢ እስካሁን ድረስ አላገኘችም ነበር፡፡ ከዚህ በኋላ ግን ቤተ ክርስቲያኗ የመልማት አቅሟን ተጠቅማ አግልግሎቷን የምትደግፍበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡

**ስምዐ ጽድቅ፡- የደብረ ዕንቍ ልደታ ለማርያም ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን በመሠራት ላይ ይገኛልና አሁን በምን ደረጃ ላይ ይገኛል?**

**መልአከ ሰላም ነቢየ ልዑል፡-** እንደሚታወቀው ሕንጻ ቤተ ክርስቲያኑ እጅግ ግዙፍና ዘመኑን የዋጀ ሆኖ እየተሠራ ነው፡፡ ከዚህ ቀደም የነበረው ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ለዘመኑ አገልግሎት የማይመችና ምእመናንን ቁጥር ያላገናዘበ ነበር፡፡ ያንን ከግንዛቤ በማስገባት ነው ሕንጻ ቤተ ክርስቲያኑ በምእመናን እገዛ በፍጥነትና በጥራት እየተገነባ ያለው፡፡ በደብሩ የሚሠራው የመስቀል ፕሮጀክትና ሕንጻ ቤተ ክርስቲያኑም በጠንካራ ሕንጻ አሠሪ ኮሚቴ እየተመሩ ያሉ ሲሆን የሕንጻ ቤተ መቅደሱ ሥራ በቁሳቁስ እጥረት ምክንያት ለሁለት ዓመታት ያህል የቆመ ቢሆንም በአሁኑ ወቅት ግን አስፈላጊው ቁሳቁስ ተሟልቶለት ሥራው እየተከናወነ ይገኛል፡፡ ነገር ግን ቀጥታ ከመንግሥት በመጣ ትዕዛዝ የመስቀል ፕሮጀክቱ ፳፬ ሜትር ከደረሰ በኋላ ግንባታው እንዲቆም ተደርጓል፡፡ ግንባታው እንዲቀጥልም አስፈላጊውን ሁሉ ጥረት እያደረግን እንገኛለን፡፡

**ስምዐ ጽድቅ፡- በደብሩ ሲከናወን የነበረው በዓይነቱ ልዩ የሆነው የመስቀል ፕሮጀክት ሥራ በምን ምክንያት እንደቆመ ቢገልጹልን?**

**መልአከ ሰላም ነቢየ ልዑል፡-** የመስቀል ፕሮጀክቱ ትልቅ ዓለማ ይዞ ሲሠራ የነበረ ቢሆንም በተለያዩ ምክንያቶች በአሁኑ ሰዓት ሥራው ቆሞ ይገኛል፡፡ ሥራው በቤተ ክርስቲያኗ ሕጋዊ ይዞታ ላይ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ የመንግሥት አካላት ለፕሮጀክቱ መልካም የሚባል አመለካከት አልነበራቸውም፡፡ በዚህ የተነሣ የመንግሥት አካላት በፕሮጀክቱ ሥራ ላይ ሲሳተፉ የነበሩ ባለሙያዎችን ጨምሮ ሌሎች የሚመለከታቸው አካላትን አስረውብን ነበር፡፡ ይሁን እንጂ የታሰሩት ሰዎች ምንም አይነት የወንጀል ተሳትፎ ያልነበራቸው በመሆኑና ይልቁንም “ፈቃድ የሌለው ሕንጻ እየገነባችሁ ነው” በሚል ሰበብ ብቻ የታሰሩ በመሆኑ ባደረግነው ጥረት ብዙም ሳይቆዩ ከእስር ሊፈቱ ችለዋል፡፡ የመስቀል ፕሮጀክቱ ፍጹም ሕጋዊና በቤተ ክርስቲያን ሕጋዊ ይዞታ ላይ እየተገነባ መሆኑን የመንግሥት አካላቱ ቢረዱም ነገር ግን ሆን ብለው ሥራውን ለማስተጓጓል አልመው እየተንቀሳቀሱ መሆኑን ተረድተናል፡፡ እኛም በቤተ ክርስቲያን ይዞታ ላይ የሚከናወኑ ማንኛውም ፕሮጀክቶች እንዲቀጥሉ ጥረት በማድረግ ላይ እንገኛለን፡፡ እንደሚታወቀው ቤተ ክርተስቲያን በሕጋዊ ይዞታዋ ላይ ለምታከናውናቸው ማንኛውም የግንባታ ሥራዎች መንግሥታዊ የግንባታ ፈቃድ ጠይቃ አታውቅም፤አያስፈልግምም፡፡ እውነታው ይህ ሆኖ ሳለ ቤተ ክርስቲያን በይዞታዋ ላይ የምትገነባው የመስቀል ፕሮጀክ ፈቃድ የለውም በሚል ሰበብ ሥራው እንዲቆም ተደርጓል፡፡ ከዚህ ቀደም ቤተ ክርስቲያናችን የተለያዩ ፕሮጀክቶችን ተግባራዊ ስታደርግ ራሷ ባላት መዋቅር በሚሰጥ ፈቃድ ትሠራለች እንጅ አንድም ጊዜ መንግሥትን የግንባታ ፈቃድ ጠይቃ አታውቅም፡፡

እስካሁን ድረስ የፕሮጀክቱ ሥራ የቆመው የመንግሥት አመራሮች የሚሰጡን የግንባታ ፈቃድ ካለ እንዲሰጡን በተደጋጋሚ ጥያቄ ብናቀርብላቸውም ምንም አይነት አጥጋቢና ተገቢ ምላሽ ሊሰጡን ባለመቻላቸው ነው፡፡ አንዳንድ በቤተ ክርስቲያን ጉዳይ ላይ የሚቆረቆሩ አካላት በፕሮጀክቱ ሥራ መቆም ዙሪያ ጠቅላይ ሚንስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድን በግል አናግረዋቸው እርሳቸውም ግንባታው እንዲቋረጥ እንዳላዘዙ ነግረዋቸዋል፡፡ ጠቅላይ ሚንስትሩ ይህንን ቢሉም ግንባታውን ስንጀምር ግን ግብረ ኃይል ወድያው ያስቆመናል፡፡ በዚህ የተነሣ አሁን ግራ በተጋባ ሁኔታ ውስጥ እንገኛለን፡፡ ጉዳዩ በሰላማዊ መንገድ እንዲፈታ ለቅዱስ ሲኖዶስ ከማሳወቅ በተጨማሪ የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ የሆኑት ብፁዕ አቡነ መልከጸዴቅ ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳድር ደብዳቤ ጽፈው የነበረ ቢሆንም ምንም አይነት ምላሽ አላገኙም፡፡ በተጨማሪም ከሀገር ቤት እስከ ውጭ ሀገር ድረስ ጉዳዩ ትኩረት እንዲያገኝ “ለመስቀሉ ሮጣለሁ” በሚል መሪ ሐሳብ የሩጫ መርሐ ግብር ብናዘጋጅም ሩጫው እንዳይካሄድ በተደጋጋሚ ክልከላ አድርገዋል፡፡ በመንግሥት ባለሥልጣናቱ ከልካይነት ሥራው የቆመው የመስቀል ፕሮጀክቱ ሥራ ከቆመበት

እንዲቀጥል በእኛ በኩል አስፈላጊ ናቸው ያልናቸውን የመፍትሔ ሐሳቦች በጋራ እያስቀመጥን እንገኛለን።

**ስምዐ ጽድቅ፡- የመስቀል ፕሮጀክት ሥራው ከተቋረጠበት እንዲቀጥልና በቤተ ክርስቲያኗ ሕጋዊ ይዞታ ላይ የመንግሥት አካላት እየፈጸመ ያለውን የግንባታ እንቅስቃሴ እንዲያቆሙ ቤተ ክርስቲያኗ በፍርድ ቤት በከሰሰችው መሠረት ውሳኔ ተወስኖላታልና የውሳኔው ፍሬ ነገር ምንድን ነው?**

**መልአከ ሰላም ነቢየ ልዑል፡-** በአብዛኛው በመስቀል ፕሮጀክቱ ዙሪያ ከፍተኛ ችግር ሲፈጥር የነበረው አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መንገዶች ባለሥልጣን ነው። ይህ ባለሥልጣን መሥሪያ ቤት በቤተ ክርስቲያኑና መስቀሉ በሚሰራበት ቦታ መካከል ፬ ሜትር ስፋት ያለው መንገድ እሠራለሁ ብሎ በመነሣቱ ምክንያት የመስቀል ፕሮጀክቱ ሥራ እንዲጓተትና ጭራሽም እንዲቆም አድረጎታል። ይህ አልበቃ ብሎ በአካባቢው ሁከትና ብጥብጥ ከማስነሣቱ በተጨማሪ የተለያዩ የግንባታ እንቅስቃሴዎችን ሲያደርግ ቆይቷል። ቤተ ክርስቲያንም ችግሩ በሰለጠነ መንገድ እንዲፈታ በተደጋጋሚ ጥረት አድርጋ ባለመሳካቱ ወደ ክስ አምርታለች። በክስ ሄደቱም ቤተ ክርስቲያን የሰውና የሰነድ ማስረጃዎችን አቅርባ ለተወሰኑ ወራት ክርክር ስታደርግ ከቆየች በኋላ የኢፌዴሪ የመጀመሪያ ፍርድ ቤት የልደታ ምድብ ፲፮ኛ ፍታብሔር ችሎት ሰኔ ፳፬ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም ብይን ሰጥቷል። ብይኑም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መንገዶች ባለሥልጣን ከሁከትና ብጥብት ተግባሩ እንዲቆጠብ እና ከግንባታ እንቅስቃሴው እንዲታቀብ የሚል ነው።

ይሁን እንጂ በስም የተጠቀሰው ባለሥልጣን መሥሪያ ቤት ከተጠቀሱት ሕገወጥ ድርጊቶቹ ይቆጠብ እንጅ አሁንም ድረስ በመስቀል ፕሮጀክቱ ሥራ ላይ ምንም አይነት የተሰጠ ብይን የለም። ይህ በመሆኑም ፕሮጀክቱ በተያዘለት ጊዜ ተጠናቆ አገልግሎት መስጠት ሲችል ሆን ተብሎ ግንባታው ከቆመበት እንዳይቀጥል መደረጉ እኛን አገልጋዮችና ምእመናንን በእጅጉ ያሳዘነ ጉዳይ ሆኗል። የግንባታ ፈቃድ እንዲሰጠን አሁንም ድረስ በተደጋጋሚ መንግሥትን እየጠየቅን እንገኛለን። የመስቀል ሥራው የማይቀር ቢሆንም ከመንግሥት ጋር አላስፈላጊ ክርክር ውስጥ ከመግባትና በወጣት ልጆቻችን ላይ ዳግም እስራትና እንግልት እንዳይደርስባቸው በማሰብ እንዲሁም ሥራው ከቆመበት እንዲቀጥል በመፈለጋችን የመንግሥትን የመጨረሻ ውሳኔ በትዕግሥት እየጠበቅን እንገኛለን።

**ስምዐ ጽድቅ፡- የመስቀል ፕሮጀክቱ በውስጡ ምን ምን ነገሮች ያካትታል? ለቤተ ክርስቲያንና ለሀገር የሚኖረው ጠቀሜታስ ምንድን ነው?**

**መልአከ ሰላም ነቢየ ልዑል፡-** ከፕሮጀክቱ ዲዛይን መረዳት እንደሚቻለው ፕሮጀክተቱ ለሀገርና ለቤተ ክርስቲያን የሚጠቅሙ በርካታ ነገሮች እንደተካተቱበት መናገር ይቻላል። ይህ ፕሮጀክት ለተለያዩ ሃይማኖታዊና ማኅበራዊ አገልግሎቶች የሚውል ሃያ አምስት ሺህ ሰዎችን መያዝ የሚችል አንፊ ቲያትር ያለው፣ ስምንት ጉባኤ ቤቶችን የያዘ፣ ከሦስት ሺህ በላይ ሰዎችን የሚይዝ ዘመናዊ አዳራሽን ያካተተ፣ የሱስ ማገገሚያ ማእከል ያለው፣ ሙዚዬም፣ ግሪን ኤሪያ እንዲሁም ግንባታው የተቋረጠውን ፷፬ ሜትር ርዝመት ያለውን መስቀል ያካተተ ነው። የመስቀል ፕሮጀክቱ ተሠርቶ ሲጠናቀቅ ለቤተ ክርስቲያን ብሎም ለሀገራችን የገቢ ምንጭ ሆኖ ሊያገለግል የሚችልና በተለይ መስቀሉ የሀገራችን ታሪካዊ ቅርስ ሆኖ ከመቀጠሉ በተጨማሪ ከተራራ ላይ ሆኖ የአዲስ አበባን ከተማ የሚባርክ ይሆናል። የመስቀል ፕሮጀክቱ ሲጠናቀቅ የቤተ ክርስቲያንን ጥበብና ዕወቀት ለዓለም የሚገልጥ ይሆናልም። እስካሁን ከሃያ ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ የተደረገበት ይህ ፕሮጀክት በመንግሥት ቀጥተኛ ትእዛዝ ከመቆሙ በፊት በከፍተኛ ጥንቃቄና ትጋት ለሃያ አራት ሰዓት ሲሠራ የቆየና እስካሁን ድረስ ዘጠኝ ሜትር ወደታች ሃያ አራት ሜትር ወደላይ ወጥቷል።

**ስምዐ ጽድቅ፡- በመጨረሻ ቀረ የሚሉት ነገር ካለ?**

**መልአከ ሰላም ነቢየ ልዑል፡-** በደብረ ዕንቍ ልደታ ለማርያም ቤተ ክርስቲያን እየተገነባ ያለው የመስቀል ፕሮጀክት ባለቤትነቱ የቤተ ክርስቲያኗ ይሁን እንጂ የሁሉም ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ሀብት ንብረት ነው። ፕሮጀክቱ የቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳይሆን የሀገርም ሀብት መሆኑን በመረዳት ሁሉም ሰው ለፕሮጀክቱ ስኬት የበኩሉን እንዲወጣ እንጠይቃለን። በተለያዩ ሙያ ዘርፍ ያሉ የቤተ ክርስቲያን ልጆችም የተለየ ድጋፍና እገዛ እንዲያደርጉ አባታዊ መልእክቴን አስተላልፈለሁ። ፕሮጀክቱ በመንግሥት ቀጥተኛ ትዕዛዝ መቆሙ ይታወሳል። ስለዚህ ይህ ፕሮጀክት ከቆመበት ለመቀጠል ተደማጭነት ያላቸው ምእመናን የበኩላቸውን ቢያደርጉ መልካም ነው። ይህ ትውልድ የተጀመረውን የሀገርና የቤተ ክርስቲያን ቅርስ እንዲጠናቀቅ የበኩሉን ድረሻ በመወጣት ታሪክ ሠርቶ ማለፍ አለበት።

ካልሆነ ግን የታሪክ ተወቃሾች እንሆናለን። መንግሥትም ሥራው እንዳይቀጥል ያለአግባብ ያቆመውን ፕሮጀክት ለሀገርና ለቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው ተረድቶ እንዲቀጥል ፈቃድ ሊሰጥ ይገባል።

# ፍልሰታ ለማርያም

እህተ ሚካኤል

***ልጆች! እንደምን ከረማችሁ? እግዚአብሔር ይመስገን እኛ በጣም ደኅና ነን፡፡ ልጆች! እንኳን ለእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ጾም (የፍልሰታ ጾም) በሰላም አደረሳችሁ! ልጆች! ዛሬ የምንጽፍንላችሁ ስለምትወዷት፣ ስለምትናፍቋትና በጉጉት ስለምትጠብቋት የፍልሰታ ጾም ነው፡፡ መቼም በዚህ የጾም ወቅት ማንም ልጅ ከቤት አይቀርም አይደል? ሁሉም ወደ ቤተ ክርስቲያን ይሄዳል በተለይ ደግሞ እናንተ ሕፃናት እጅግ እንደምትወዷት ሁሉም ሰው ያውቃልና የተባረካችሁ የተወደዳችሁ ናችሁ፡፡ እኛም ስለዚህች በጉጉት ስለምትጠብቋት ጾም እንነግራችኋለንና በጥሞና ተከታተሉን እሺ ልጆች!***

ልጆች! ጾመ ፍልሰታ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን ከእረፍቷ በኋላ ሥጋዋ ተሰውሯቸው ስለነበር የእመቤታችን ክቡር ሥጋዋን እንዲሰጣቸው ሐዋርያት የጾሙት ጾም ነው፡፡ እመቤታችን በዚህ ምድር ላይ ፷፬ ዓመት ከኖረች በኋላ ሞታለች፣ ከዚያም ተነሥታለች

እንዲሁም ወደ ሰማይ አርጋለች፡፡ ‹‹ፍልሰታ›› የሚለው ቃልም ‹‹ፈለሰ›› ከሚለው የግዕዝ ቃል የተገኘ ሲሆን መለየት፣ ወደሰማይ ማረግ የሚል ትርጉም አለው፡፡ ‹‹ጾመ ፍልሰታ›› የእመቤታችን ድንግል ማርያምን ከሙታን ተለይቶ መነሣት እንዲሁም ወደ ሰማይ ማረግን ያመለክታል፡፡

ልጆች! ጾመ ፍልሰታ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በዐዋጅ ከተደነገቻቸው ሰባቱ አጽዋማት አንዱ ሲሆን ሁሉም የቤተ ክርስቲያን ልጅ ትንሽ ትልቅ፣ወንድ ሴት ሳይል የሚጾመው ጾም ነው፡፡ የጾሙ ጊዜም ነሐሴ ፩ ጀምሮ ነሐሴ ፲፮ ይጠናቀቃል፡፡

ልጆች! እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከልጇ ከጌታችን ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ሠላሳ ሦስት ዓመት ከሦስት ወር እንዲሁም ከዮሐንስ ወልደ ዘብዴዎስ ዘንድ ዐሥራ አራት ዓመት ከዘጠኝ ወር ቆይታ በ፷፬ ዓመት እድሜዋ ባረፈች ጊዜ ቅዱሳን ሐዋርያት የእመቤታችንን አስከሬን ይዘው ሊቀብሯት ወደ ጌቴሴማኔ ሲሄዱ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በክፋት የሰቀሉት አይሁድ ‹‹ከዚህ ቀደም ልጇ ሞትኩ ተነሣሁ ዐረግሁ እያለ ሲያውከን ኖረ አሁን ደግሞ እሷ ሞትኩ ተነሣሁ ዐረግሁ እያለች ልታውከንም አይደል! እንነሣና አስከሬኗን እናቃጥለው!" በማለት በተንኮል ተነሣሡ፡፡ አስከሬኗን ይዘው ወደ ጌቴሴማኔ እየሄዱ ሳለም ታዖፋንያ የሚባለው ክፉ ሰው አስከሬኗን ከእጃቸው ሊነጥቅ ሲል የእግዚአብሔር መልአክ እጆቹን በሰይፍ ቆረጣቸው፡፡ የእመቤታችንን ሥጋና ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስን ወስደው በገነት ከዕፀ ሕይዎት ዛፍ ሥር አስቀመጧቸው፡፡

ልጆች! ሐዋርያት የእመቤታችንን ሥጋዋን አግኝተው በጌቴሴማኔ የመቃብር ስፍራ ይቀብሯት ዘንድ በዐረፈች በስምንተኛው ወር ከነሐሴ ፩ ቀን ጀምሮ እስከ ነሐሴ ፲፬ ቀን ድረስ ሁለት ሱባዔ በጾም በጸሎት ተወስነው ቆዩ፡፡ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዐሥራ ዐራተኛው ቀን የእናቱን የቅድስት ድንግል ማርያምን ሥጋዋን ሰጥቶአቸው በጌቴሴማኔ ቀበሯት፡፡ ልጆች! እመቤታችን ያረፈችው በጥር ፳፩ ቀን ሲሆን የተቀበረችው ደግሞ በነሐሴ ፲፬ ቀን ነው ይህም የሆነው

እመቤታችን ሥጋዋ ለስምንት ወር ያህል በዕፀ ሕይወት ዛፍ ሥር አርፎ ስለነበረ ነው፡፡ ለዚህም ነው አባቶቻችን ‹‹ ሞት በጥር በነሐሴ መቃብር›› የሚሉት፡፡



ሐዋርያት የእመቤታችንን አስከሬን ወስደው በጌቴሴማኔ ሲቀብሩ ከዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት አንዱ ቶማስ አገልግሎት ነበረበትና በሥፍራው አልተገኘ ነበር፡፡ በሦስተኛው ቀንም አመቤታችን ከሙታን ተለይታ ተነሥታ ወደ ሰማይ ስታርግ ሐዋርያው ቶማስ ከሀገረ ስብከቱ በደመና ተጭኖ ወደ ኢየሩሳሌም ሲመጣ እመቤታችንን አገኛት፡፡ እርሱም ‹‹ከዚህ በፊት የልጅሽን ትንሣኤ ሳላይ ቀረሁ አሁን ደግሞ ያንችን ትንሣኤ ሳላይ ቀርቼ ነበር›› ብሎ አዘነ፡፡ እመቤታችንም ከእርሱ በስተቀር ትንሣኤዋን ማንም እንዳላየ ነግራው ለምልክትም የተገነዘችበትን ሰበን(የመግነዝ ጨርቅ) ሰጥታው ወደሰማይ ዐረገች፡፡

ሐዋርያው ቶማስም ወደ ሐዋርያት በተመለሰ ጊዜ የእመቤታችንን ነገር ጠየቃቸው እነሱም ሥጋዋን ጌታ ሰጥቷቸው እንደቀበሩአት ነገሩት፡፡ መቃብሯን ካላየሁ አላምንም በማለቱም ወደ ጌቴሴማኔ ይዘውት ሄደው መቃብሩን ሲከፍቱ የእመቤታችን ሥጋዋ ባለመኖሩ እጅግ ደነገጡ፡፡ ሐዋርያው ቶማስም ‹‹አታምኑኝም ብዬ እንጂ ተነሥታ ዐርጋለች›› አላቸው ለምልክትም የተገነዘችበትን ሰበን አሳያቸው፡፡ ከዚያም በኋላ ለበረከት ይሆናቸው ዘንድ ሰበኑን ተካፍለው ወደየሀገረ ስብከታቸው ሄዱ፡፡

ልጆች! ዛሬ በቅዳሴ ጊዜ ዲያቆኑ በሚይዘው የመጾር መስቀል ላይ በሁለት መተላለፊያ ቀዳዳዎች ውስጥ ገብቶ የምናየው ጨርቅ ይህ ሐዋርያት ለበረከት የተካፈሉት የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የመግነዝ ጨርቅ ወይም ሰበን ምሳሌ ነው፡፡

ልጆች! ሐዋርያት በዓመቱ ለወንጌል አገልግሎት ከሄዱበት ተሰብስበው ‹‹ሐዋርያው ያየው የትንሣኤሽና የዕርገትሽ በረከት አይቅርብን›› ብለው ከነሐሴ ፩ ጀምሮ ሱባዔ ያዙ በነሐሴ ፲፮ ቀንም ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከእናቱ፣ ከመላእክትና ከቅዱሳን ጋር በመሆን በሐዋርያት መካከል ተገኘ፡፡ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን መንበር፤ ሊቀ ሐዋርያት ቅዱስ ጴጥሮስን ተራዳኢ ካህን፤ ሊቀ ዲያቆናት ቅዱስ እስጢፋኖስን ዲያቆን አድርጎ ቀድሶ ካቆረባቸው ለጸሎታቸው መልስ ትንሣኤዋንና እርገቷን እንደገና አሳያቸውና እናቱ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ወደ ሰማይ አረገች፡፡

ልጆች! ቅድስት ቤተ ክርስቲያንም የሐዋርያትን ፈለግ በመከተል ምእመናን ትልቅ ትንሽ ሳይሉ ከእመቤታችን በረከትን እንዲያገኙ ይህንን ጾም እንዲጾሙ ዐውጃለች፡፡ በተለይ ሕፃናት በብዛት ይህንን ጾመ ፍልሰታን ይጾሙታል በዚህም እናንተ ሕፃናት እድለኞች ናችሁ በርቱ እሺ ልጆች!

**የእመቤታችን ድንግል ማርያም ምልጃዋና በረከቷ አይለየን አሜን!**

**ምንጭ ፡-**
ውዳሴ ማርያም ትርጓሜ
ነገረ ማርያም

# የሁለት ዓለም ሰዎች

ኪኑኪሩ ከአዲስ አበባ

የሰዎች ሕይወት በብዙ ውጣ ውረድ ውስጥ ያልፋል። ለክርስቲያኖች ደግሞ የዚህ ዓለም ሕይወት እጅግ ፈታኝ ነው፡፡ በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ ብሎ ጌታችን ለደቀ መዛሙርቱ የተናገረው ቃል እያንዳንዷ ክርስቶሳዊት ነፍስ የምታልፍበትን የፈተና ሰንሰለት የሚጠቁም ነው፡፡

የክርስቲያኖች ተስፋ ከትንሣኤ ሙታን ጀምሮ መንግሥቱን እስከመጨረስ ነው፡፡ ይህ ዓለም ጊዜያዊ መሆኑን እንደሚያልፍ ጌታና ሐዋርያት አስተምረውናል፡፡ ነገር ግን ከዓለም እንድንወጣ ሳይሆን በዓለም ውስጥ ሳለን ከዓላማችን፣ ከሕይወት ጉዟችን የሚያናጥቡ ፈተናዎችን የሚያፈራርቅብንን የዚህ ዓለም ወጥመድ እየሰበሩ ባለድል መሆን የክርስቲያኖች ዋንኛ ተግባር ነው፡፡

ይህ ሆኖ ሳለ በፈተና መውደቅና መነሣት ያለ ነው፡፡ ክርስቲኖች ንጹሕ ቅዱስ የሆነ ሕይወትን ገንዘብ አድርገው እንዲኖሩ ተጠርተዋል፡፡ ከዚህ መንገድ ወጥቶ መሰበር ሲያጋጥም በንስሓ ሕይወት እየተጠገኑ ወደ መንገዱ መመለስ የግድ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ድካምን፣ ውድቀትን የማመንና የትሕትና ሕይወት ያስፈልገዋል፡፡

ከዚህ ውጪ ሆነን ግን ወድቀን ሳለን እንደቆምን የምንቆጥር ከሆነ ሌሎችን እንሰናከላለን፡፡ የዚህ ጽሑፍም ዋነኛ ትኩረት በመንፈሳዊና በሥጋዊ ሕይወት መካከል፣ በሰማያዊና ምድራዊ አኗኗር መካከል፣ በጽድቅና በኃጢአት መካከል ሆኖ ለመኖር የሚሹ ወገኖች ላይ የምንታዘባቸውን ጉዳዮች መጠቃቀስ ነው፡፡

አንዳንድ ወገኖች በቤተ ክርስቲያን ተገኝተው በአዳባባይ አገልግሎታቸው እስከሚገለጥ ድረስ በተለያዩ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎቶች ውስጥ በኩረ ምእመናን ሆነው፣ ተሰልፈው እናገኛቸዋለን፡፡ ቤተ ክርስቲያን ሕንፃ ግንባታ፣ ለተለያዩ ፕሮጀክቶች ገቢ በማሰባሰብ፣ በበዓላት ጊዜ ምእመናንን በማስተባበር፣ በሰንበት አገልግሎት ጊዜም በዓውደ ምሕረት ላለው የማስተባበር ሥራ በግንባር ይታያሉ፡፡ ይህንን ተግባር በቤተ ክርስቲያን እያከናወኑ ለቤተ ክርስቲያን በአገልግሎታቸው ብርሃን የሆኑ እንዳሉ ሁሉ ለትዝብት የሚጋለጡት ጥቂቶች አይደሉም፡፡ የእግዚአብሔር ቤት አገልጋይ ሆነው ስማቸው በመንፈሳዊነት የሚጠራ ግብራቸው ከመንፈሳዊነት የራቀ በእግዚአብሔር ብቻ ሳይሆን በሰው ዘንድ የተገለጠ ብዙዎች ናቸው፡፡ የሚያደርሱት ጥፋትም ከባድ በመሆኑ አካሄዳቸው ትኩረት ይሻል፡፡

ይህ ሥራቸው በምእመናን ዘንድ ክብር አስጥቷቸው ሲያበቃ፣ እነዚህኑ ሰዎች በአልኮል መጠጥ ቤቶች ፊት ለፊት ሆነው፣ በዘፈንና በጭፈራ አደባባዮች ፊት ለፊት ተዋናይ ሆነው፣ በመሥሪያ ቤቶቻቸው በሥራ ትጋትና ታማኝነት የሚወገዙ ሆነው ለሌሎች እንቅፋት በመሆን፣ ሌሎችን በማሳዘን የሚታወቁ … ወዘተ ደግሞ ይታያሉ፡፡

እንዲህ ዓይነት ሰዎች ብዙዎች ታዝበዋቸው ለምን ማለታቸው አልቀረም፡፡ የክርስትና ሕይወት እምነትም መታመንም የሚፈልግ ነው፡፡ ‹‹መልካሙን የእምነት ገድል ተጋደል፥ የተጠራህለትንም በብዙም ምስክሮች ፊት በመልካም መታመን የታመንህለትን የዘላለምን ሕይወት ያዝ፡፡›› እንዲል፡፡ (፩ኛ ጢሞ ፮፥፲፪)

ክርስትና በቦታ የተወሰነ የአኗኗር መዘበራረቅን አይቀበልም፡፡ በአጸደ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሰንመላለስ የምናሳየውን መታመን ከቅጽረ ቤተ ክርስቲያን ውጪም ማሳየት (መሆን) ይጠበቃል፡፡ በመንፈሳውያን ጉባኤ፣ በታማኝ ክርስቲያኖች ዘንድ የሚታይብን ጠባይ ዓለማውያን ባሉበትና በሚበዙበት ሥፍራም መታየት አለበት፡፡ ‹‹የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም በጎና ደስ የሚያሰኝ ፍጹምም የሆነው ነገር ምን እንደ ሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ፡፡›› (ሮሜ ፲፪፥፪) ተብለናል፡፡

በጊዜ ውስጥ የሚዘበራረቅ የክርስቲያን አኗኗር ተቀባይነት የሌለውና የግብዝነት ነው፡፡ በጨለማና በብርሃን በጠዋትና በማታ የሚታይብን ጠባይ ከክርስቲያናዊ ሕይወት አፈንግጦ ቢታይ ለትዝብት የሚዳርግ ነው፡፡ ሰዎችንም ያሰናክላል፡፡ ‹‹በእኔም ከሚያምኑ ከእነዚህ ከታናናሾቹ አንዱን የሚያሰናክል ሁሉ፥ የወፍጮ ድንጋይ በአንገቱ ታስሮ ወደ ጥልቅ ባሕር መስጠም ይሻለው ነበር፡፡›› (ማቴ ፲፰፥ ፮)

ጠዋት በቤተ ክርስቲያን በቀናነቱ የታየ ሰው ማታ በምሽት በክፋት ቢታይ ለሚያዩት ሰዎች ማሰናከያ ሊሆን ይችላል፡፡ በአገልግሎቱ ወይም በክርስቲያናዊ ማንነቱ ላይ ታማኝነት ያጣል፡፡

በዚህ መንገድ መጠመድ ማሰናከያ ከመሆኑም በላይ ለዚያች ነፍስ ለራሷ ጭንቀትና ውዝግብን ትጋብዛለች፡፡ ማመንታት ሌላውን ብቻ ሳይሆን ራስንም ይጎዳልና፡፡ ቃለ እግዚአብሔርን ለመስፋፋት የፈቀደ ሰው ዓለምን ለመምሰልም ፍላጎት

ካደረበት በተግባርም የሚራመድበት ከሆነ ነፍሱን ያስጨንቃል፡፡ መዋለል ከንቱነትን ያስከትላል፡፡

‹‹በራድ ወይም ትኩስ እንዳይደለህ ሥራህን አውቃለሁ፡፡ በራድ ወይም ትኩስ ብትሆንስ መልካም በሆነ ነበር፡፡ እንዲሁ ለብ ስላልህ በራድም ወይም ትኩስ ስላልሆንህ ከአፌ ልተፋህ ነው፡፡›› (ራእይ ፫÷፲፭-፲፮) እንደተባለው ይሆንበታል፡፡

ሌላው ደግሞ ከክርስቶስ የተቀበልነውን የምስክርነት ሕይወት አደራ መዘንጋት ነው፡፡ በተለይ ከምእመናን መካከል ጎልተው የሚታዩ ከሆነ ከእነርሱ አርአያነት ይጠበቃል፡፡ እንዲህ ዓይነት ሰዎች ‹‹ብርሃናችሁ በሰው ሁሉ ፊት ይብራ፤....›› ‹‹እናንተ የምድር ጨው ናችሁ፤ ጨው አልጫ ቢሆን በምን ይጣፍጣል›› ብሎ ጌታችን ከተናገረው ቃል ያፈነገጠ አካሔድ ስለሚከተሉ አደራ መግፋት ይሆንባቸዋል፡፡

በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ውስጥ አለሁ በሚል እየተገ ያሉ ሰዎች መልሰው በማይገባ ቦታ ሆኖ መታየት ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ከፍተኛ መሰናክል ያመጣል፡፡ እነዚህ ሰዎች የሚፈጥሩት የሕይወት መዛነፍ ሰዎችን ደግሞ ትዝብት ላይ ከመጣል ባሻገር የብዙዎችን ሕይወት መጉዳቱ አይቀሬ ነው፡፡ ለእነዚህ ሰዎች የሚሻለውም መምረጥ ነው፡፡

ከምርጫ ውጪ አደባልቆ የአመንዝራነትን ሕይወት ማስተናገድ ውጤቱ ከንቱነት ነው፡፡ ሰዎች የሁለቱም ዓለም ሰው ለመሆን ፍላጎት ካደረባቸውና በተግባርም እንዲሁ ከሆኑ በክርስትና መነጽር ውድቀት ሆኖ የሚታይ ነው፡ ፡ ምርጫ እንጂ ማጫፈር ተቀባይነት የለውም፡፡ መንፈሳዊ ሕይወትን መምረጥ ዘላለማዊነትን ገንዘብ ማድረግ አንድ ምርጫ ሲሆን፣ በዚህ ዓለም ጠፊ አላፊ ነገር መደሰትና ዘላለማዊ ሕይወትን ማጣት ሌላ ምርጫ ነው፡፡ ምርጫው በሕይወት የመኖርና የሞት ምርጫ ነው፡፡

የማይተባበሩ ነገሮችን እንዲተባበሩ ማድረግ የሚያስተዛዝብ ነው፤ መጽሐፍ እንዳለ ‹‹ለእግዚአብሔር ቤተ መቅደስም ከጣዖት ጋር ምን ኅብረት አለው? እኛ የሕያው እግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ነንና እንዲሁም እግዚአብሔር ተናገረ እንዲህ ሲል፦ በእነርሱ እኖራለሁ በመካከላቸውም እመላለሳለሁ፥ አምላካቸውም እሆናለሁ እነርሱም ሕዝቤ ይሆናሉ፡፡ ስለዚህም ጌታ፦ ከመካከላቸው ውጡና የተለያችሁ ሁኑ ርኵስንም አትንኩ ይላል፤ ሁሉንም የሚገዛ ጌታ፦ እኔም እቀበላችኋለሁ፥ ለእናንተም አባት እሆናለሁ እናንተም ለእኔ ወንድ ልጆችና ሴት ልጆች ትሆናላችሁ ይላል፡፡ ጽድቅ ከዓመፅ ጋር ምን ተካፋይነት አለውና? ብርሃንም ከጨለማ ጋር ምን ኅብረት አለው? ክርስቶስስ ከቤልሆር ጋር ምን መስማማት አለው? ወይስ የሚያምን ከማያምን ጋር ምን ክፍል አለው?›› (፪ኛ ቆሮ ፮÷፲፭)፡፡

በመስፍኑና በነብዩ ኢያሱ ቃልም ‹‹እግዚአብሔርንም ማምለክ ክፉ መስሎ ቢታያችሁ፥ አባቶቻችሁ በወንዝ ማዶ ሳሉ ያመለኩአቸውን አማልክት ወይም በምድራቸው ያላችሁባቸውን የአሞራውያንን አማልክት ታመልኩ እንደ ሆነ፥ የምታመልኩትን ዛሬ ምረጡ፡፡ እኔና ቤቴ ግን እግዚአብሔርን እናመልካለን፡፡›› (ኢያ ፳፬÷፲፭) ማለት ያስፈልጋል፡፡

ክርስቲያኖች በዚህ ዓለም የተሰጠን አደራ በዓለም ያሉትን ለእግዚአብሔር የማስገዛት በቃሉ የመሳብ ኃላፊነት ነው፡፡ ይህ ተልእኳችንም የሕይወታችንም የደስታችንም ምንጭ ነው፡፡ ለሰዎችም ያለንን ፍቅር መግለጫ ነው፡፡ ለእግዚአብሔርም ያለንን ታማኝነት የምንገልጠው በዚህ ነው፡፡

መንፈሳዊውን ቃል፣ ሰማያዊውን ሕይወት ልንሰብካቸው የሚገባቸውን ሰዎች እነርሱ የተላበሱትን ዓለማዊነት ተላብሰን እነርሱን መስለን የበለጠ የምናጠፋቸው ከሆነ ድርብ በደል ይሆናል፡፡ ከኃጢአት ወደ ጽድቅ፣ ከሁከት ወደ ሰላም መምጣት ያለባቸውን ሰዎች ማረጋጋት ማዳን ሲገባ እነርሱ ባሉበት ማጥ ውስጥ ገብቶ መታየት ትልቅ ስህተት ነው፡፡ ‹‹አንዳንዶችንም ከእሳት ነጥቃችሁ አድኑ፥...›› (ይሁዳ ፩÷፳፪) አለን፤ ሰዎችን እሳቱን ለምደው እንዲኖሩ ራሳችን መገፋፋት ከባድ በደል ነው፡፡

ክርስቲያኖች ይልቁንም አገልጋይና በአገልግሎቱ ውስጥ ጎልተው የሚታዩ ሰዎች ምእምናንን ከማሰናከል በተጨማሪ ክርስትናን፣ ቤተ ክርስቲያንንና የጌታዋን የመድኃኒቷን የኢየሱስ ክርስቶስን መንገድ ማሰደብ ይሆንባቸዋል፡፡ ‹‹በእናንተ ሰበብ የእግዚአብሔር ስም በአሕዛብ መካከል ይሰደባልና›› ተብሎ እንደ ተጻፈ፡፡ (ሮሜ ፪÷፳፬) ዳግመኛም ቅዱስ ጴጥሮስ ‹‹በእነርሱም ጠንቅ የእውነት መንገድ ይሰደባል፡፡›› (፪ኛ ጴጥ ፪÷፪) ያለው ይሆንባቸዋል፡፡

ሌላው አሳሳቢው ነገር ሌሎችም ተተኪ አገልጋዮችና ከምእመናን መካከል ንቁ ሆነው በአገልግሎቱ አጋዥ ለመሆን የሚሰለፉ ሰዎች የእነርሱን አርኣያ ሊከተሉ መቻላቸው ነው፡፡ ለእነርሱ የጥፋት መልክ አሊያም የበጎ አገልጋይነት ገጽታ ሆኖ ሊሣል ስለሚችል ብርቱ ጥንቃቄ ያስፈልጋል፡፡

እነርሱም ከትዝብትና ከፍርድ እንዲወጡ ሌሎች ብርቱ አገልጋዮች የመምከር የመገሰጽ ኃላፊነት አለባቸው፡፡ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን፣ቃለ እግዚአብሔርን ቁጭ ብለው እንዲማሩም ዕድል ማግኘት አለባቸው እንላለን፡፡

# ለሚጠቅም ነገር ወደ ‹‹ጠንቅዋዮች›› ብሔድስ?

***ውድ የስምዐ ጽድቅ አዘጋጆች እንዴት አላችሁ? እኔ እግዚአብሔር ይመስገን ደኅና ነኝ፡፡ በአንድ ጉዳይ ግራ ተጋብቻለሁ፤ ይኸውም ጓደኛዬ ስለጥንቆላ ያላት ግንዛቤ በእምነት ሕይወቴ ውስጥ ፈተና እያመጣብኝ ነው፡፡ ‹‹ለበጎ ነገር መጠንቆልም ሆነ ማስጠንቆል ችግር የለውም›› ትለኛለች፡፡ ሀብትን ለማግኘት፣ ጤንነትን ለማግኘት፣ እውነትን ለማወቅ... አዋቂዎች ዘንድ መሄድ ችግር የለውም ብላ ታምናለች፡፡ ‹‹ሰዎቹ ክፉ ሥራ ሠሩ የሚባለው ሌሎች ሰዎችን የሚጎዳ ሲሠሩ ብቻ ነው›› ብላ ታስባለች፡፡ ይህ ነገር ብዙ ጊዜ የጤና ችግር ላለብኝ ለእኔ ፈተና ሆኖብኛል፡፡ በደዌ ብዙ ጊዜ ከምሠቃይ ፈውስ የሚሰጠኝ ከሆነ ብሔድ ምን ችግር አለው ብዬ አስባሁ፡፡ በተለይ በጣም በሚያመኝ ጊዜ ‹‹ከፈወሱኝ ብሔድ ምን ችግር አለው›› ብዬ ማሰብ አዘወትራለሁ፡፡ ሃይማቴን እንድቀይር ካላስገደደኝ ‹‹ያውቃል›› የሚባለው ሰው ዘንድ ብሔድ ችግር የለውም ብዬ ለማሰብ እየተገደድሁ ነው፡፡ ከሥቃይ መውጣትን እግዚአብሔር ይቃወማል ብዬ አላስብም እናንተ ምን ትመክሩኛላችሁ?***

ውድ ጠያቂያችን! በመጀመሪያ ለገጠመዎ የእምነት ውዝግብ መፍትሔ ይሰጡኛል ብለው በማመን ጥያቄዎን ወደ እኛ በመላክዎ እናመሰግናለን፡፡ ጥያቄዎ የእርስዎ ብቻ ሳይሆን ተመሳሳይ አረዳድ ያላቸው የሌሎችም ሰዎች ነው ብለን እናምናለን፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ሰዎች አዋቂዎች እያሉ የሚጠሯቸው የጥንቆላ ሥራ የሚሠሩ ሰዎች ተግባር በቤተክርስቲያን ትምህርት ባዕድ አምልኮ ከሚባሉት መካከል በእጅጉ የተወገዘ ተግባር ነው፡፡

ጠንቋዮች ከጥንት ጀምሮ በሰው ልጆች ሕይወት ውስጥ የሰይጣንን ጣልቃ ገብነት የሚያስከትሉ አደገኛ የጥፋት ሠራተኞች ናቸው፡፡ በየዘመኑ ግን የተለያየ ስም እየሰጡ የሚያምኗቸው ሰዎች መልካም የሚመስል ስም እየሰጡ ሌሎችን ሲያዘናጉባቸው ታይቷል፡፡ ብዙ ጊዜ አዋቂ ፣ ጠቢባን ፣ መድኃኒተኞች ወዘተ በሚል ሽፋን አደገኛ ወጥመድ የሚዘረጉበት መንገድ አለ፡፡

በእርስዎም በኩል ጓደኛዎ ልትሰብክልዎት የፈለገችው በዚሁ መንገድ ነው፡፡ ለምሳሌም በግብጽ ሀገር ከእግዚአብሔር መንፈስ ውጪ ሆነው ‹‹እናውቅልሃለን›› የሚሉ ሰዎችን በተለየ ስም ይጠሯቸው እንደነበር እናስተውላለን ‹‹ፈርዖንም ጠቢባንን፣ መተተኞችን፣ ጠራ፡፡ የግብጽም ጠንቋዮች በአስማታቸው እንዲሁ ደግሞ አደረጉ፡፡ እያንዳንዳቸውም በትራቸውን ጣሉ፤ እባቦችም ሆኑ፤ የሙሴ በትር ግን በትራቸውን ዋጠች፡፡›› ይላል (ዘፀ ፯፥ ፲፩) እነዚህ የፈርዖን ምርጦች ጠቢባን ይባሉ እንጂ ሥራቸው ግን የእግዚአብሔርን መንፈስ እየተቃወሙ በሐሰት ኃይል ያላቸው እየመሰሉ ማታለል ነው፡፡ እነዚህ ኢያኔስና ኢያንበሬስ የሚባሉት የፈርዖን ጠንቋዮች በግብጽ ሀገር ሰዎች እንደ አዋቂ፣ ኃይል እንዳላቸው በጣም ይታመንባቸው ስለነበር ለፈርዖን ባለሟል እስከመሆን ደርሰው ነበር፡፡ የቤተ መንግሥቱም የኃይል ምንጭ ተደርገው ይታሰቡ ነበር፡፡ እውነተኛ የእግዚአብሔር መንፈስና ኃይል ሲመጣ ግን የእነዚህ ሰዎች አላዋቂነት፣ ማታለያ ፣ ማስመሰል ተገለጠባቸው፤ አፈሩ፡፡

ውድ ጠያቂያችን! ‹‹አዋቂዎች›› የሚባሉ ሰዎች ጊዜያዊና የማስመሰል አካሄድን በመከተል ለሰው በጎ የሚያደርጉ መስለው ይታዩ እንጂ ከሰይጣን የሚመነጭ ጊዜያዊ ማደናገሪያዎች እንጂ ዘላቂ በጎነት ያላቸውን ነገሮች ሊያደርጉ አይችሉም፡፡ እንደዚህ ዓይነት ሰዎች በእነ ዳንኤልም ዘመን የቤተ መንግሥት ባለሟል ሆነው እስከ መሥራት ይደርሱ ነበር፡፡ ናቡከደነጾር በቤተመንግሥቱ ጠቢባን፣ አስማተኞች የሚባሉ ሰዎች ነበሩት የእነዚህ አስማተኞች ማስመሰያና የውሸት ኃይል የታወቀው ፈናቡከደነጾር የእግዚአብሔር መንፈስ ያደረባቸውን እውነተኛ ሕልም ተርጓሚዎችና አስተዋዮችን ዳንኤልን፣ አናንያ፣አዛርያና ሚሳኤልን ባገኘ ጊዜ ነበር፡፡ ‹‹ንጉሡም በጠየቃቸው ጊዜ በጥበብና በማስተዋል ነገር ሁሉ በግዛቱ ሁሉ በግዛቱ ሁሉ ከሚኖሩ የሕልም ተርጓሚዎችና አስማተኞች ሁሉ እነርሱ ዐሥር አጅ የበለጡ ሆነው አገኛቸው›› (ዳን ፩፥፳) ብሎ ስለነዳንኤል ከተመሰከረው መረዳት ይቻላል፡፡

ስለሆነም እውነተኛ አዋቂ ጠቢብ እግዚአብሔር ነው፡፡ እርሱም እውነትን የሚገልጠው ለወዳጆቹና ለሚያምኑት በመሆኑ ዳንኤል እንዲህ አለ ‹‹ምስጢር የሚገልጥ አምላክ በሰማይ ውስጥ አለ›› (ዳን.፪፥ ፳፰)፡፡

ውድ ጠያቂያችን! ሀብት መስጠት፣ ጤና መስጠት፣ ዕውቀት መስጠት፣ ወዘተ የሚባሉ በጎ የሚመስሉ ነገሮችን እናደርጋለን የሚል ጠንቅዋዮች አካሄድ ለሕይወትዎ ፈተና መሆኑ አይገርምም፡፡ አደገኛው ግን እርስዎ እና ጓደኛዎ የያዛችሁት አረዳድ አደገኛ መሆኑ ነው፡፡ በጎን የሚሠራ ሁሉ ከእግዚአብሔር ነው ብሎ ማመንና ለዚህ ዓላማ ጠንቋዮችን መጠቀም ችግር እንደሌለው ማሰብ ነው፡፡፡ ሰይጣን አሳቢና በጎን የሚሠራ መስሎ የሰዎችን ሕይወት ወጥምድ ውስጥ እንደሚያስገባ ከአዳምና ከሔዋን የመጀመሪያው መታለል መረዳት ይገባል፡፡ ሰይጣን ለአዳምና ሔዋን ዕውቀትን፣ ጥበብን የሚሰጥ መስሎ ትእዛዝ እንዲያፈርሱ በጋበዛቸው ጊዜ የጠበቁትን ብልጽግና ሳይሆን ጉስቁልናና ውርደት ተሸክመዋል፡፡

ውድ ጠያቂያችን! ሰይጣን አስመሳይና አደናጋሪ መሆኑን አይርሱ፤ ዲያብሎስ ሸንጋይ መሆኑን ሐዋርያው ነግሮናል፡፡ ስለዚህ ያደረጉልን መስሎን መታለል አይገባም፡፡ በሚርት በጣዖት ማምለክ የሚመጣ ዘላቂ ጤና፣ ዘላቂ ሀብት፣ ዘላቂ ዕውቀት የለም፡፡ በዚህ መንገድ የሚገኝ ሁሉ በራስና በቤተሰብ ላይ

ፈርዶ የሚገኝ ጊዜያዊ መረጋጋት ነው፡፡ ሰይጣን ለራሱ ሳያስገዛ የሚሰጠው በጎ ነገር የለም፡፡ በሰዎች ላይ አድሮ በልዩ ልዩ መንገድ ተገዢ ያደርገናል እንጂ፡፡ (ኤፌ ፮፥፲)

ሰይጣን የሚሰጠን ነገር ሁሉ ያለዋጋ አይደለም፡፡ ነፍሳችን እንድንሰጠው ይፈልጋል፡፡ ይህንንም ጌታችንን በፈተነው ጊዜ ያለው ቃል ማስተዋል ይገባል ‹‹ዲያብሎስ እጅግ ረጅም ወደ ሆነ ተራራ ወሰደው፥ የዓለምንም መንግሥታት ሁሉ ክብራቸውንም አሳይቶ፦ ወድቀህ ብትሰግድልኝ ይህን ሁሉ እሰጥሃለሁ አለው፡፡›› (ማቴ. ፬፥፰-፱) ይላል፡፡ ሁልጊዜም ዲያብሎስ ለመስጠት ከሚገባው በጎ ከሚመስል ነገር ሁሉ ጀርባ መገዛት አለ፡፡ ሳይገዙለት የሚሰጠው ጤናም ሆነ ሀብት የለም፡፡

ውድ ጠያቂያችን! ብዙ ሰዎች ለራሳቸውና ለልጆቻቸው ጤና ብለው አዋቂዎች ወደሚሏቸው ሰዎች ሄደው ሲመለሱ በተለያዩ ጊዜያት ተመልሶ የመሄድ ግዴታ ወይም ባሉበት ‹‹ጨሌ›› እንዲሸከሙ፣ ወይም የእንስሳት ግብር እንዲያቀርቡ እንደሚታዘዙ አላስተዋሉም? ይህ ከባድ ለዲያብሎስ ተገዢነት ነው፡፡ ይህንን ባያደርጉ የሰጣቸው የመሰለቻውን ጤና፣ የሰጣቸው የመሰላቸውን ሀብት መልሶ ይነፍጋቸዋል፡፡ ጦርነትም ያውጅባቸዋል፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር በንስሓ ሕይወት ቆመው በጾም በጸሎት ለመጋደል የወሰኑ ያሸንፉታል፤ ሌሎችን ግን ይጎዳቸዋል፡፡

ስለዚህ ጠያቂያችን የሚሉትን በጎ የሚመስል ነገር ሁሉ ሰጪና ነሺ መስሎ በሆነ ኃይል የሚሠራ ሰው መኖሩ ሊስያገርምዎት ይገባም፡፡ ‹‹የእርሱ መምጣት በተአምራት ሁሉና በምልክቶች በሐሰተኛ ድንቆችም በዓመፅም መታለል ሁሉ እንደ ሰይጣን አሠራር ነው ›› (፪ኛ ተሰሎ ፪-፱) የተባለው በመጨረሻው ዘመን ስለሚመጣው ሐሳዌ መሲህ የተባለውን በማስተዋል ጉዳዩን መረዳት ይቻላል፡፡ ሰይጣን ሐሰተኛ ድንቆችን ለብዙዎች መጥፋት ምክንያ እንዲሆኑ ይጠቀምባቸዋል፡፡ እንዲህ ያለ መንፈስ ‹‹እሳትንም እንኳ ከሰማይ ወደ ምድር በሰው ፊት እስኪያወርድ ድረስ ታላላቆችን ምልክቶች ያደርጋል፡፡ በአውሬውም ፊት ያደርግ ዘንድ ከተሰጡት ምልክቶች የተነሣ በምድር የሚኖሩትን ያስታል፤›› (ራዕ ፲፫ ፥ ፲፫) እንደተባለው ሰይጣናዊ ማታለያዎች ለብዙዎች መጥፋት ምክንያት ናቸው፡፡

ውድ ጠያቂያችን! እርስዎ እንደገለጹልን ከእምነትዎ መውጣት አይፈልጉም፡፡ ይህ በውስጥዎ ያለ ጽኑ አቋም ከሆነ ለዲያብሎስ ወጥመድ ብር አይክፈቱ፡፡ የባልንጀራን የጥፋት ምክር አይስሙ፡፡ በራስዎ ማስተዋልም አይደገፉ፡፡ የሚሻለው ቃለ እግዚአብሔርን መስማት ነው፡፡ የቤተ ክርስቲያን ትምህርት መከተል ነው፡፡

የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ደግሞ ለዲያብሎስ ሽንገላ ፊት አለመስጠት ነው፡፡ ዲያብሎስ ሁሌም የሚያጠምደን በደካማ ጎናችን ነው፡፡ ጠያቂያችን አጋጠመኝ ያሉትን የጤና መታወክ ለብዙዎች መታለል እንደ አንድ ደካማ ጎን የሚጠቀምበት ነገር ነው፡፡ ሰው ሥጋው ሲታመም ከሥቃይ ለማረፍ መፈለጉ ተፈጥሯዊ ነው፡፡ ማንም ቢሆን ከሥቃይ መፈወስ ይሻል፡፡ ይህ የሰዎች ብርቱ ፍላጎት መሆኑና ሰውም ከሥጋ ሕማም ሊጠቃ የሚችል ፍጥረት መሆኑን ዲያብሎስ ያውቃል፡፡ በዚህም ምክንያት በኃጢአታችን ምክንያት ወይም ደግሞ በብርቱ ተጋድሏችን ምክንያት ወይም እግዚአብሔር ስለሚሰጠን ጸጋ ያደረብንን ደዌ ሰይጣን ሊጠቀምበት ይፈልጋል፡፡

ውድ ጠያቂያችን! በእንዲህ ዓይነት የፈተና ጊዜ ከአንድ ክርስቶሳዊ ክርስቲያን የሚጠበቀው ጽናትና ከእግዚአብሔር የሚሰጥ ፈውስን ነው፡፡ እግዚአብሔር ደግሞ ለደዌያችን ፈውስ አድርጎ መድኃኒቶችን ሰጥቶናል፡፡ ከምድር የሚገኙ ከዕፅዋት ወይም ከእንስሳት ወዘተ ተዋጽኦ የተዘጋጁ መድኃኒቶችን ብንጠቀም የሚከለከል አይሆንም፡፡ ይህ ካልሆነ ደግሞ በንስሓ ሕይወት ውስጥ ሆኖ እግዚአብሔር ፈውስን እንዲልክልን ሥጋ ወደሙ መቀበል፣ መማጸን ጠበል መጠመቅ ፣እምነት መቀባት ወዘተ ያስፈልጋል፡፡ ይህ በቅዱሳን ሕይወት ውስጥም ነበር፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹የሥጋዬ መውጊያ እርሱም የሚጎስመኝ የሰይጣን መልእክተኛ ተሰጠኝ፡፡ ከእኔ እንዲለይ ሦስት ጊዜ ጌታን ለምንሁ›› ብሏል፡፡ (፪ኛቆሮ ፲፪፥ ፱)

እንዲህም ጻልዮ ፈወስን ባለማግኘቱ ወደ ሌላ መንገድ አላዘነበልም፡፡ ጌታ ለጸጋ የሚሆን ደዌ እንደሰጠው ባወቀ ጊዜ ደዌውን ተሸክሞ ጸና እንጂ፤ ክርስቶስን አልተወም፡፡ ከዚህ መማር ይገባል፡፡ ደዌያት እንዲርቁልን መጸለይ ሌሎች መንፈሳዊ የምንላቸው መፍትሔዎች ሁሉ መጠቀም ነው፡፡ ይህ ካልሆነ ግን ከሰይጣን ከሚገኝ ፈውስ የሚመስል የነፍስ ደዌን የመሸከም ነገር መሸሽ ይገባል፡፡

ውድ ጠያቂያችን! ከክፉ የሚገኝ በጎነት የለም ከጨካኝ የሚጠበቅ ርኅራኄም የለም፡፡ ሁሉም ማስመሰል ነው፡፡ ከኩርንችት በለስ አይጠብቁ፡፡ ‹‹አዋቂዎች›› የሚባሉ ጠንቋዮች ሁሉ የዲያብሎስ ሠራተኞች ናቸው፡፡ ዲያብሎስን ፍጹም ይቃወሙ፡፡ መቼም ቢሆን የእምነት ሐሳብዎን አይስበሩ፡፡ ጊዜያዊ በሆኑ የዚህ ዓለም ጥቅምና ዕረፍቶች አይዘናጉ፡፡ በቅዱስ ጳውሎስ ቃል እንምከርዎ፤ ‹‹ዘመኑ አጭር ሆኗል፤ የሚያለቅሱም እንደማያለቅሱ፣ ደስ የሚላቸውም ደስ እንደማይላቸው፤ የሚገዙም ምንም እንደሌላቸው በዚህችም ዓለም የሚጠቀሙ በሙሉ እንደማይጠቀሙባት ይሁኑ፤ የዚህች ዓለም መልክ አላፊ ነውና›› (፩ኛ ቆሮ ፯፥ ፴፩) ፡፡

ስለዚህ ‹‹የሚሠሩት በጎ ነውና...›› ብለው የተሳሳቱ ሰዎች ‹‹አዋቂ›› ወደሚሏቸው ጠንቋዮች ለመሄድ ልብዎ አያዘንብል፡፡ ይህ ሥራ የታወቀ የሥጋ ሥራ ነው፡፡ ኃጢአት ነው፡፡ ‹‹ጣዖትን ማምለክ ሟርት የሥጋ ሥራ ነው›› (ገላ. ፭ ፥፲፱) ከዚህ በፊትም ላሰቡት ወደ መምህረ ንስሓዎ ሔደው ንስሓ ይግቡ፡፡ ሕይወትዎን በእምነት ይኑሩ፡፡

***ወስብሐት ለእግዚአብሔር***